
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የላ/ደ/ት/ቅዱስ ሚካኤል እና ቅዱስ ጊዮርጊስ
ቤተክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት

# ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር



ማውጫ

መግቢያ ....3
**ምዕራፍ አንድ**
፩. የክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር መግቢያ ....4
፩.፩ ሥነ-ምግባር ማለት ምን ማለት ነው? ....4
፩.፪ የሥነ-ምግባር ትምህርት መምር ለምን አስፈለገ? ....5
**ምዕራፍ ሁለት**
፪. ክርስትያናዊ ሥነ-ምግባር ለሰው ልጅ ድኅነት ያለው አስፈላጊነት ....7
**ምዕራፍ ሶስት**
፫. ሕግጋተ እግዚአብሔር ....13
፫.፩ ኢ-ጽሑፋዊ ሕግ ....14
፫.፩ ጽሑፋዊ ሕግ ....14
**ምዕራፍ አራት**
፬. አሥርቱ ትዕዛዛት ....15
፬.፩ የአሥርቱ ትዕዛዛት ዓላማ ....16
፬.፪ የአሥርቱ ትዕዛዛት አከፋፈል ....16
፬.፪.፩ ከፍቅር አንጻር ሲከፈሉ ....16
፬.፪.፪ ከተነገሩበት አንጻር በ2 ይከፈላሉ ....16
፬.፪.፫ ከአፈጻጸማቸው አንጻር ሲታይ በ3 ይከፈላሉ ....16
፬.፫.የአሥርቱ ትዕዛዛት ዝርዝር ጥናት ....17
፬.፫.፩ ትዕዛዝ ፩ “ከኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁንልህ” ዘጸ 20፥2 ....17
፬.፫.፪ ትዕዛዝ ፪ “የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም ከንቱ አትጥራ” ....19
፬.፫.፫ ትዕዛዝ ፫ “የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ” ....22
፬.፫.፬ ትዕዛዝ ፬ “እናትና አባትህን አክብር ....23
፬.፫.፭ ትዕዛዝ ፭ “አትግደል” ዘጸ 20፥13 ....24
፬.፫.፮ ትዕዛዝ ፮ “አታመንዝር” ዘጸ 20፥14 ....25
፬.፫.፯ ትእዛዝ ፯ “አትስረቅ” ዘጸ 20፥15 ....27
፬.፫.፰ ትዕዛዝ ፰ “በባለንጀራህ ላይ በሀሰት አትመስክር” ዘጸ 20፥16 ....29
፬.፫.፱ ትዕዛዝ ፱ “የባለንጀራህን ቤት አትመኝ” ዘጸ 20፥17 ....30
፬.፫.፲ ትዕዛዝ ፲ "ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ" ዘሌ. 19፥18 ....31
**ምዕራፍ አምስት**
፭. ህግጋተ ወንጌል ....33
ዋቢ መጻሕፍት ....37

## መግቢያ

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ በ2፥18-20 «እምነት ያለምግባር ምግባር ያለ እምነት ባዶ፥ የሞተ ነው፡፡» ብሎ ጽፏል፡፡ ማንም እምነት አለኝ የሚል ምግባር ከሌለው እምነቱ በራሱ ከንቱ ነው፡፡ በምግባር የሚኖርም እምነት ከሌለው እንዲሁ ነው፡፡ አንድ ክርስቲያን ክርስቲያን ለመባል እምነትና ምግባርን አስተባብሮ መያዝ ይኖርበታል፡፡

ክርስቲያን በሕይወት በሚኖርበት ዘመን እግዚአብሔርን የሚያስደስት፣ በሰዎች ዘንድ ታማኝ፣ በሚኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ተወዳጅ መሆን አለበት፡፡ ይሄ ሊሆን የሚችለው በምግባር ታንጾ ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ሌላው አንድ ክርስቲያን የክርስትና ህይወቱ የሚበራ መሆን አለበት፡፡ በቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል በ5፥16 "...ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ" ሲል ጌታ አስተምሯል፡፡ ይህ ማለት አንድ ክርስቲያን በሚያሳየው ምግባሩ ማለትም የአለባበስ፥ የአነጋገር፥ የአካሄድ (የአረማመድ)፥ የጾም፥ የጸሎት፥ ምጽዋት ወዘተ በእነዚህ ሕይወቶች ሲኖር ለሌሎች በአርያነት የሚንጸባርቅ፣ የሚያበራ እና የሚያስተምር ይሆናል፡፡

ክርስቲያናዊ ስነ-ምግባር መሠረቱ አሥርቱ ትዕዛዛትና ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ናቸው፡፡ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ መገዛት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ ሕግጋት ደግሞ እግዚብሔር ለሙሴ በመለኮታዊ ኃይሉ ጽፎ የሰጠው ሲሆን ማንኛውም ክርስቲያን ሊተገብራቸውና ሊኖርባቸው ይገባል፡፡ የክርስቲያን ሥነ-ምግባር መሠረቱ ፈሪሃ እግዚአብሔር ነው፡፡ በፈሪሃ እግዚአብሔር የሚኖር ሰው ከመስረቅ፣ ከማመንዘር፣ ከመግደል፣ በሐሰት ከመማል፣ ሰውን ከመበደል በአጠቃላይ በኃጢአት ከመኖርና ኃጢአትን ከመስራት ይቆጠባል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# ፩. የክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር መግቢያ

*ውድ አንባብያን በዚህ ምዕራፍ ስለ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር ምንነት፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር መማር የሚሰጠው ጥቅም እና አስፈላጊነት እንማራለን:: መልካም ቆይታ*

## ፩.፩ ሥነ-ምግባር ማለት ምን ማለት ነው?

ሥነ-ምግባር ማለት ከሁለት ጥምር የግእዝ ቃላት የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም **"ሥነ"** የሚለው ቃል ሠነየ፣ አማረ፣ መልካም ሆነ፣ ተዋበ ማለት ሲሆን **"ምግባር"** ማለት ደግሞ ገበረ፣ ከሚለው ግሥ የተገኘ ሥራ፣ ፈጠራ፣ ክንውን፣ ተግባር ማለት ነው:: በአጠቃላይ ሥነ-ምግባር ማለት ያማረ የተዋበና መልካም ስራ ማለት ነው::
*"መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያመሰግኑት ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ"* በማለት ሥነ-ምግባር ያለው ክርስቲያን በእሱ መልካም ስራ ሰማያዊው አባቱ (አምላኩ) እግዚአብሔር እንደሚመሰገን ጌታችን የተናገረው ቃል ነው:: *ማቴ. 5፣16*

አንድን ሥነ-ምግባር ለመለካት፤ አግባብ ነው ወይም አይደለም ለማለት መለኪያ ያስፈልገዋል:: ሰዎች ከራሳቸው የእውቀት እና የማስተዋል ደረጃ በመነሳት አንድን ምግባር ትክክል ነው ወይም አይደለም ሊሉ ከዛም አልፈው ለሌላውም ሊያስተምሩ ይችላሉ:: አንድ ክርስትያን ግን አንድን ምግባር የሚመዝነው ወይም የሚለካው በራሱ ፈቃድ እና ስሜት ወይም በሌሎች ሀሳብ በመመራት ሳይሆን በክርስትና የሥነ-ምግባር መለኪያዎች መሆን ይገባዋል:: የክርስትና የሥነ- ምግባር መለኪያዎች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁም ከመጽሐፍ ቅዱስ ተወጣጥተው ተሰፍፍተው የተዘጋጁ ቀኖናዎች ፣ ደንቦች እና ትውፊቶች ናቸው:: ስለዚህ ክርስትያናዊ ስነ ምግባር ስንል በነዚህ ቅዱሳን መጻህፍት ከተጻፉት መመሪየዎች፣ ህጎችና ሃሳቦች ጋር የተስማማ ያማረ፣ የተዋበ፣ ሥን ያለው ምግባር ማለት ነው::

*"እግዚአብሔር ይነግሮሙ ለህዝቡ በመጽሐፍ፤እግዚአብሔር ለህዝቡ በውስጥዋም ለተወለዱ አለቆችዋ በመጽሐፍ ይነግራቸዋል" መዝ86፥6* እንደሚል የክብር ባለቤት እግዚአብሔርም ለሰው ልጆች የህይወት መመሪያና የሥነ ምግባር መማሪያ እንዲሆኑ መጻህፍትን ሰጥቷል:: ለነዚህ በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት ለሰጣቸው ትእዛዛት መሪ ቀዳሚና ማጠቃለያ አድርጎ ያስቀመጠው ደግሞ *ፍቅርን* ነው:: ይኸውም ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ (የባልንጀራ ፍቅር) ተብለው ይታወቃሉ::

*"አምላክህ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም ኀይልህ ውደድው:: ታላቂቱና የመጀመሪያይቱ ትእዛዝ ይህቺ ናት:: የምትመስላት ሁለተኛቱም ባልንጀራህን አንደራስህ ውደድ የምትል ናት:: ኦሪትና ነቢያት ሁሉ በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸንተዋል::" ማቴ22፥37-40*

ከትእዛዛት ሁሉ የሚበልጠው እግዚአብሔርን መውደድ ሲሆን እግዚአብሔርን የመውደድ የመፍራትና የማክበር ማረጋገጫው ደግሞ እግዚአብሔር በራሱ አርአያና ምሳሌ የፈጠረውን የወደደውንና አንድ ልጁን ለሞት የሰጠለትን ሰውን መውደድ ነው:: ሰውን የመውደድ መገለጫውም "ለራስ ሊደረግ የሚወዱትን ለሌላው ማድረግ፤ በራስ ሊደረግ የማይወዱትን በሌላው ከማድረግ መጠበቅ ነው::" ማቴ7፥12

በየዘርፉ ለሚተነተነው ክርስትያናዊ ስነ ምግባር ሥሩ መሠረቱ ይህ ነው:: በአስርቱ ትእዛዛትን በስድስቱ ቃላተ ወንጌል የተዘረዘሩት መመሪያዎች ሁሉ ከዚህ ዐቢይ የሥነ-ምግባር መርህ አንጻር በየዘርፉ የሚተረጎሙ ናቸው:: ሰውንና እግዚአብሔርን የሚወዱ ክርስትያኖች፦ "አባትን እናትህን አክብር፣ አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር፣ የባልንጀራህን ሚስቱን ቤቱን ሀብቱን ንብረቱን አትመኝ፣ ባልንጀራህን አንደራስህ ውደድ" የሚሉትን ትእዛዛት ይጠብቋቸዋል ይጠነቀቁባቸዋል::

ሕግ አዋቂ የነበረ አንድ ሰው *"መምህር ሆይ ምን ሥራ ብሠራ የዘለዓለም ሐይወትን እወርሳለሁ?"* ብሎ ላቀረበው ጥያቄ ጌታ ሲመልስ *"አምላክህ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ሰውነትህ፣ በፍጹም ኃየልህ፣ በኃሳብህም ሁሉ ውደድ፤ ባልንጀራህንም እንደራስህ ውደድ" አለው:: ጠያቂው ግን ራሱን ሊያከብር ፈልጎ "ወንድሜ ማነው?"* በማለት ደግሞ ላነሳው ጥያቄ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ በሚወስደው መንገድ ስጓዝ ወንበዴዎች ባደረሱበት አደጋ የተጎዳውን የተለያዩ መንገደኞች እያዩት አልፈው ሲሔዱ እሱ ግን ሳያልፍ በችግሩ በደረሰለትና ተገቢውን እርዳታ ባደረገለት በጎ ሳምራዊ ሰው አንጻር "ሂድ አንተም እንደዚሁ አድርግ" ተብሎ የተሰጠው መልስ ለክርስትያኖች ሁሉ የክርስትያናዊ ሥነ-ምግባር መመሪያ ነው::

እግዚአብሔርንና ሰውን ከመውደድ የወጣ የሥነ ምግባር ትምህርትና መንገድ የለም፡፡ በጎ ስራ ሁሉ ሰውንና እግዚአብሔርን በመውደድ ይፈጸማል፡፡ ሰውን መውደድ ሲባል ራስንም ይጨምራል፡፡ ለሌላው በጎ ማድረግ ወይም በሌላው ላይ ክፉ ከማድረግ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የራስንም ሰውነት ሕይወትና ክብር ከሚጎዱ ሰብአዊ ክብርንና ሰብአዊነትን ከሚያዋርዱ ጎጂ ልምዶች አስጸያፊና አጥፊ ድርጊቶች መራቅ መጠበቅ፤ ሕይወትን በቅድስና መንፈስን በንጽህና መያዝ ነው፡፡1ቆሮ3፥16-17 ሰውነታችን የእግዚአብሔር ማደሪያ(ታቦቱ) ስለሆነ ቤቱን በንጽህና መጠበቅ መጠንቀቅ የሥነ ምግባር ትልቁ ክፍል ነው፡፡

## ***፩.፪ የክርስትያናዊ ሥነ-ምግባር ትምህርት መማር ለምን አስፈለገ?***

የክርስትያናዊ ሥነ-ምግባር ትምህርት መማር ያስፈለገበት መሠረታዊ ምክንያት ክርስትያን ተብለን የምንጠራ በአምልኮተ እግዚአብሔር የምንኖር ህዝበ ክርስቲያኖች ሁሉ ከአንድ ክርስትያን የሚጠበቁ ምግባራት ምን እንደሆኑ አንድናውቅና በክርስትና የምግባር መለኪያዎች መሰረት ህይወታችንን መምራት እንድንችል ነው፡፡ በዚህም ከግላዊ ስሜቶችና ማኆቶች በዓለምም ካሉ የተሳሳቱ አመለካከቶች እርቀን በአንድ ሐሳብ እና በአንድ ልቦና ልውል እግዚአብሔር በሚፈቅደው ክርስቲያዊ ጉዞ መጓዝ አንችላለን፡፡

በሃይማኖት የሚኖር ሰው በምግባሩ የተመሠከረለት ሊሆን ይገባል፡፡ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር መማር መልካም ሥነ ምግባር ያለው፣ ለራስም ሆነ ለወገን ጠቃሚ የሆነ ዜጋን አልፎም መሪን ለመፍጠር ይጠቅማል፡፡ የሰው ልጅ ከሌሎች የእግዚአብሔር ፍጥረታት ጋርም አንኳን ተስማምቶ መኖር የሚችለው አካሄዱ በአግባብ እና በሥርዓት ሲሆን ነው፡፡ የሰው ልጅ ልቅና መረን ያጣ ጉዞ ከተፈጥሮ ጋርም ሲያጋጨው እንመለከታለን፡፡ አባታችን አዳም በገነት ትዕዛዘ እግዚአብሔርን አክብሮ በሚኖርበት ዘመን(ከሰባት ዓመት በላይ) ከሌሎች ፍጥረታት ጋር ተስማምቶ ይኖር እንደነበር ገደለ አዳም በተባለ በቤተ-ክርስቲያን መጽሐፍ ላይ ተጠቅሷል፡፡ በመልካም ምግባራቸው አምላካቸውን ያስደሰቱ ቅዱሳን ይህ ጸጋ ተመልሶላቸው ከፍጥረታት ሁሉ ጋር ተስማምተው ሲኖሩ ከዛም አልፈው ፍጥረታትንም ሆነ ተፈጥሮን ሲያዝዙ እንመለከታለን፡፡ ስለዚህ በክርስትያናዊ ሥነ ምግባር የታነጸ ህዝብ ማፍራት አይደለም ከሰው ጋር ከተፈጥሮም ጋር ተስማምቶ ለመኖር አስፈላጊ ነው፡፡

በዚህ ትምህርት ላይ ክርስትያናዊ ሥነ-ምግባር ለሰው ልጅ ድህነት ያለው አስፈላጊነት፣ ስለ ህግ ምንነት እና የህግጋት አይነቶች፣ ከነዚያም መካከል በዋነኝነት ስለክርስትያናዊ የሥነ-ምግባር ህግጋት ወይም ህግጋተ እግዚአብሔር ማለትም፡- ሕገ ልቦና፣ ሕገ ኦሪት፣ ሕገ ወንጌል፣ ምግባራተ ወንጌል እና አንቀጸ ብጹአንን እንመለከታለን፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ፪.ክርስትያናዊ ሥነ-ምግባር ለሰው ልጅ ድኅነት ያለው አስፈላጊነት

ይህን ክርስትያናዊ ሥነ-ምግባር የተሰኘውን ትምህርት ስንማር ቅድሚያዉን የሚወስደዉ ስለ ነገረ ድኅነት ቤተ ክርስትያናችን የምታስተምረዉን ትምህርት በዉል መገንዘብ ይሆናል፡፡

ቤተ ክርስትያናችንን ከሌሎች የእምነት ድርጅቶች በዋናነት ከሚለያት ነገሮች አንዱ የመዳን ትምህርቷ ነው፡፡ በተለያየ አጋጣሚ "ድነኃል?" ወይም "ድነሻል?" የሚሉ በድኅነታችን ዙርያ ከሌሎች የእምነት ድርጅት ተከታዮች የሚጠየቁ ጥያቄዎችን አስተናግደን ይሆናል፡፡ *"መዳን"* የሚለው ቃል እንደ አገባቡ የተለያየ መልእክት ወይም ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ለምሳሌ *"መዳን"* የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ከተለያዩ አይነት ችግሮችና ጥፋቶች ስለ መዳን ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ዘፍ19፤ ዘፍ6-9፤ 2ነገ8፥7-10፤ ማቴ8፥23-27፤ የሐዋ27፥31 ጌታችን በዘመነ ስጋዌው ከልዩ ልዩ አይነት ደዌና ችግር ያዳንቸው ብዙዎች ነበሩ፡፡ በአጠቃላይ ከተለያዩ ክፉ ነገሮች መዳን (2ጢሞ4፥18) እንዲሁም ከደዌ መፈወስም ፤ እነዚህ ሁሉ *"መዳን"* ተብለው ተገልጸዋል፡፡

ሆኖም በነገረ ድኅነት ትምህርት *"መዳን"* ስንል እነዚህንና መሰሎቹን ማለታችን አይደለም፡፡ ከላይ የተጠቀሱት መዳኖች ጠቃሚ ቢሆኑም ጊዜያዊና በዚህ ዓለም ተወስነው የሚቀሩ ናቸው፡፡ በነገረ ድኅነት ትምህርት ውስጥ *"መዳን"* ስንል ግን የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በማፍረሱ ምክንያት ከደረሰበት ተደራራቢ ውድቀቶችና የባህርይ መጎሳቆሎች በእግዚአብሔር ልዩ ምክር በኢየሱስ ክርስቶስ ስጋዌ በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠውን መዳን ማለታችን ነው፡፡

የሰው ልጅ *"በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ"* ተብሎ አስቀድሞ ተነግሮት የነበረው የሞት ማስጠንቀቂያ በገቢር ተፈጽሞበት፤ የሞት ተገዢ ሆኖ ነበር (ዘፍ2፥17)፡፡ ማለትም ሲሞት ነፍሱ በጻዕር ተለይታው ሥጋው ወደ መቃብር ነፍሱ ወደ ሲዖል ትወርድ ነበር፡፡ ጌታችን ግን የኛን ስጋ በመዋሐድ ሞታችንን ሞቶ ሞትን አጠፋልን፤ የመቃብርን ይዞ የማስቀረትና ሰውነታችንን የማፍረስና አበስብሶ ለዘለዓለም የማስቀረት ኃይል ድል በማድረግ የትንሳኤያችን በኩር ሆኖ በመነሳት የትንኤን ተስፋ ሰጠን፤ ሞትን በትንሳኤ ለወጠልን፡፡ ስለዚህ ስጋችን በመቃብር ለዘለዓለም በስብሶ አይቀርም፤ ነፍሳትም ሁሉ ወደ ሲዖል አይወርዱም፤ መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሳኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሳኤ ይነሳሉ (ዮሐ 5፡29)፡፡ ስለዚህ መዳን በእግዚአብሔር ቸርነት ለሰው ሁሉ የተሰጠ ጸጋ ነው፡፡

*". . . እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ስልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፣ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፣ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ" ዕብ 2፡14-15*

በኦርቶዶክዊ አስተምህሮ መዳን ስንል በኃጢአት ከመጣው ሞትና ቅጣት ማምለጥና ነጻ መውጣት ብቻ ሳይሆን በዚህ ላይ ሐዲስ ተፈጥሮን ገንዘብ ማድረግን፣ እግዚአብሔርን ማወቅን እና በቅድስናና እግዚአብሔርን በመምሰል ከመልክአ እግዚአብሔር(Image) ወደ አርአያ

እግዚአብሔር(Likeness) የሚደረግ ዕድገትን - ሱታፌ አምላካዊን (Theosis - የጸጋ አምላክነትን ገንዘብ የማድረግ ሂደትንም) የሚይዝ ሰፊና ጥልቅ ነገር ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ሰዉ ለድኅነት የእግዚአብሔር ጸጋ ያስፈልገዋል፡፡

የእግዚአብሄር ጸጋ ለሰዉ ልጆች ሁሉ ያለምንም ዋጋ እንዲሁ ስለወደደን ብቻ በአንድያ ልጁ አማካኝነት የተሰጠን ስጦታ ነዉ፡፡ *«ያዳነን በቅዱስ አጠራሩም የጠራን እግዚአብሔር ነው፡፡ ይህም እንደራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ስራችን መጠን አይደለም»* 2ኛ ጢሞ1÷9፤ ቲቶ3÷4፤ዕብ9÷2 *«ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ማንም እንዳመካ»* ኤፌ2÷9፡፡ ይህ ስጦታ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመ የድኅነት ስራ ነው፡፡ የጌታችን የማዳን ስራ በመልዕልተ መስቀል ባፈጸም ኖሮ የሰው ልጅ በጎ ስራ ብቻውን ለድህነት አያበቃውም፡፡

*“ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ፥ እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፤”* ቲቶ 3፡4-5

የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰው ሁሉ በነጻ የተሰጠ ስጦታ ነው፡፡ይህን ስጦታ ተቀብለን እንንከባከበዋለን እንኖርበታለን እንጂ ድኅነት “በማመን ብቻ የሚገኝ ነዉ”፤ “ይህ ድህነታችንም ቅጽበታዊ እንጂ ሂደት አይደለም” የሚልን ከፍሎ አማኝነትን ቤተክርስትያናችን አታስተምርም፡፡ በተቃራኒም ግማሹን ከፍሎ በስራችን ብቻ እንድናለን አንልም፡፡ ነገር ግን ለአንድ ሰው ድኅነት ከእግዚአብሔር ጸጋ በተጨማሪ የሰዉ ልጅ በጎፍቃድም ያስፈልጋል፡፡ አንድ ሰው ሳይፈልግ መፈለጉንም በተግባር ሳይገንጽ ለዚያም ሳይጋደልበት ድህነትን አያገኝም፡፡ *“ሁልጊዜ እንደ ታዘዛችሁ. . .በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ”* ፊል 2፡12፡፡ ስለሆነም የሰው ልጅ ሱታፌ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ የሰዉ በጎፍቃድ የሚገለጸዉ ደግሞ ይህን የእግዚአብሄርን ስጦታ ተቀብሎ የዲቢሎስን ፍቃድ ለመቃወም እና የእግዚአብሔርን ፍቃድ ለመፈጸም በሚያደርገዉ ተጋድሎ ነዉ፡፡ በእግዚአብሔር በኩል ሰውን ለማዳን አስፈላጊ የሆነው ነገር ሁሉ - የእግዚአብሔር ድርሻ - ተፈጽሟል፡፡ አሁን የሚቀረው የእያንዳንዳችን ድርሻ ብቻ ነው፡፡ *“አብረንም እየሠራን የእግዚአብሔርን ጸጋ በከንቱ እንዳትቀበሉ ደግሞ እንለምናለን፤”* (2ቆሮ 6፡1)፡፡ይህም ማለት እግዚአብሔር ያደረገልንን የማዳን ጸጋ ለመቀበል ከእኛ የሚጠበቀውን ነገር (ምንም እንኳንየምናደርገው ነገር ለጸጋው የሚመጥንና እዚህ ግባ የሚባል ባይሆንም) ሳናደርግ እንዳንቀር ነው፡፡ ከእርሱ የሚጠበቅበትን ለማይፈጽም ሰው የእግዚአብሔር ሰውን ማዳን ብቻ በራሱ እንዲድን አያደርገውም፡፡ *“ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም፤”* (ዕብ12፡4)

አንድ ሰው ለመዳን የሚከተሉትን መፈጸም ይጠበቅበታል ፦

1. እምነት (ማመን) - ማመን ስንል እግዚአብሔር አንድ መሆኑን፤ በአንድነቱ ውስጥ(እርሱ ራሱ እንዳስተማረን) ልዩና የማይመረመር ሦስትነት ያለው መሆኑን፤ ከሦስቱ አካል አንዱ አካላዊ ቃል ወልድ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው መሆኑን፤ ሥግው ቃል ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ከመወለድ ጀምሮ ለሰው ሲል ያደረገውን - መጠመቁን፣ ዞሮ ማስተማሩን፣ መከራ መቀበሉን፣ በራሱ ፈቃድ ለኛ ሲል መሞቱን፣ መቀበሩንና በሦስተኛው ቀን መነሣቱን እና በአርባኛው ቀን ወደ ቀደመ ክብሩ ማረጉን . . . ሁሉ ማመን ለመዳን አስፈላጊ ነው፡፡

   ይህን ለማያምን ሰው ልክ የሰው ድኅነት እንዳልተፈጸመና ገና እንዳልዳነ ይሆንበታል፡፡ ይህም ማለት በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምን ሰው አሁን እየኖረበት ያለው ዘመን ዘመነ ወንጌል ዓመተ ምህረት ቢሆንም እርሱ ግን በዘመነ ኦሪት በዓመተ ፍዳ እንደ ነበሩት ሰዎች ይሆናል ማለት ነው፡፡

   *“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና . . . በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።” ዮሐ 3፡16-18*

   *“በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም፡፡” ዮሐ 3፡36*

*"እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።" ዮሐ 5፡24*

ጌታችን *በልጁ የሚያምን* አለ እንጂ *"ማመን ብቻ"* አላልም፡፡ ማመን (እምነት) መሰረት ነው፤ ነገር ግን *"እምነት ብቻ"* የሚል ትምህርት ጌታም ሆኑ ሐዋርያት አላስተማሩም፡፡ *"በእምነት መዳን"* እና *"በእምነት ብቻ መዳን "* በእጅጉ የተለያዩ ነገሮች ናቸውና፡፡ በእምነት መሰረትነት ላይ የሚያስፈልጉ ሌሎች ነገሮችም አሉ፡፡ *"ወንድሞቼ ሆይ፥ እምነት አለኝ የሚል፥ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን?" ያዕ2፡14*

2. ለመዳን መሰረታዊ የሆኑ ምስጢራትን መፈጸም ያስፈልጋል ፦ እነዚህም በመጀመርያ ጥምቀት፣ ሜሮንና ቁርባን ሲሆኑ ከዚህ በኋላ በሕይወታችን ለሚያጋጥሙን ውድቀቶች ደግሞ ንስሐ አስፈላጊ ነው፡፡

*ምስጢረ ጥምቀት* - በጥምቀት ከክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ጋር እንተባበራለን፡፡ *". . . ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤" ሮሜ6፡5*

*"ጴጥሮስም፦ ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።" ሐዋ2፡38*

*"ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና።" ገላ3፡27*

*"እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።" ዮሐ 3፡5*

*"ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።" ማር16፡16 "ያላመነ ያልተጠመቀ ግን ይፈረድበታል"* ያላለበት ምክንያት ያላመነ ሰው ሊመጠመቅ የሚፈልግበት ምክንያት ስለሌለ ነው፡፡

*"ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል . . ." 1ጴጥ3፡21*

*ምስጢረ ሜሮን* - ለተጠመቁ ሰዎች ከጥምቀት ቀጥሎ ወድያውኑ የሚፈጸም ምስጢር ነው፡፡ ይህም በቅዱስ ቅባት መቀባትን የሚያመለክት ምስጢር ሲሆን፤ በዚህም ተጠማቂው አባቱን እግዚአብሔርንና ፍቅሩ በውስጡ የሚሳልበትን ጸጋ ያገኛል፡፡

*"እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፥ ሁሉንም ታውቃላችሁ። . . . እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፥ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፥ እውነተኛም እንደ ሆነ ውሸትም እንዳልሆነ፥ እናንተንም እንዳስተማራችሁ፥ በእርሱ ኑሩ።" 1ዮሐ2፡20፤27*

*ምሥጢረ ቁርባን* - አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለሙ ሁሉ ቤዛ ይሆን ዘንድ የተወደደ መስዋዕት አድርጎ ያቀረበው ራሱን ነው፡፡

*"ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና። እንካችሁ፥ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፦ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።" ማቴ26፡26-28*

*"ኢየሱስም መለሰ፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የምትፈልጉኝ እንጀራን ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ ነው እንጂ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም። ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ . . . የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፡፡ አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም፤ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ*

*እንጀራ ይህ ነው። ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።" ዮሐ6፡26-27፣ 49-51*

*"እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።" ዮሐ6፡53-56*

*ምስጢረ ንስሐ* - አንድ ሰው በህይወቱ ለሚፈጽው ስህተትና ኃጢአት ራሱን ወቅሶ፣ ዳግም ላለመፈጸም ወስኖና ተናዝዞ በንስሐ ወደ አምላኩ መመለስ አለበት፡፡

*"ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ።"ሉቃ13፡3*

*"ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤"የሐዋ2፡38*

*"አምነውም ከነበሩት እጅግ ሰዎች ያደረጉትን እየተናዘዙና እየተናገሩ ይመጡ ነበር።" የሐዋ19፡18*

*"ኢያሱም አካንን፦ ልጄ ሆይ፥ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ፥ ለእርሱም ተናዘዝ ያደረግኸውንም ንገረኝ አትሸሽገኝ አለው።" ኢያ7፡19*

*"ለማንም እንዳትናገር ተጠንቀቅ፥ ነገር ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ" ማቴ8፡4*

3. *ለመዳን በክርስትያናዊ ስነ-ምግባርና ተጋድሎ፤ በተቀበልነውም ጸጋ መጽናት ያስፈልጋል* - መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መዳን የሚያስተምረው ትምህረት ሁለት ነገሮችን ማዕከል ባደረገ መልኩ ነው፡፡ በአንድ በኩል ድኅነት እና ዘላለማዊ ህይወት በሰው ጥረትና አቅም የተገኘና የሚገኝ ሳይሆን በእግዘአብሔር ቸርነት የተሰጠ የነጻ ስጦታ(ጸጋ) መሆኑን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ የመዳን ጸጋ ለመካፈል እያንዳዱ ሰው ከማመን ጀምሮ ከምስጢራተ ቤተ ክርስትያን ጋር በዚህ ዓለም ይኖርበት ዘንድ እስከ ተሰጠው የህይወቱ ፍጻሜ ድረስ በክርስትያናዊ ስነ-ምግባር መጽናትና መጋደል ያለበት መሆኑን ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል ያስፈልገናል፡፡ ለመዳን ከእምነትና ምስጢራትን ከመፈጸም ጋር ኃጢአትን መቃወም፣ በስነ-ምግባር መኖርና ደም እስከማፍሰስ መጋደል ያስፈልጋል፡፡ የዚህም የክርስትያናዊ ስነ-ምግባር ትምህርት ዓላማም ለድኅነታችን እጅጉን አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች መካከል አንዱና ወሳኝ ስለሆነው ክርስትያናዊ ስነ-ምግባር በእርሱም እንዴት መኖር እንደሚቻል ማሳወቅ ነው፡፡

*"እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል፤ በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል፤ ለዓመፃ በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙትና በአድመኞች ላይ ግን ቍጣና መቅሠፍት ይሆንባቸዋል።" ሮሜ2፡6-10*

*"ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል" የሐዋ14፡22*

*"ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።" ያዕ2፡26*

*"ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም፤" ዕብ12፡4*

*"ከክፉ ሽሽ፥ መልካምንም አድርግ ለዘላለምም ትኖራለህ።" መዝ37፡27*

*ለመዳን ሐይማኖትና ምግባር የማይነጣጠሉ ነገሮች መሆናቸውን ሐዋርያው ያዕቆብ ሲያስረዳ - "ወንድሞቼ ሆይ፥ እምነት አለኝ የሚል፥ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን? . . . እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል። አንተ ከንቱ ሰው፥ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ*

*መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን? አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ፥ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን? መጽሐፍም። አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ። ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ። እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን? ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።" ያዕ2፡14-26*

እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ አድናል ማለት እዳችን ተከፍሏል፣ የድኅነት መንገድ ተከፍቷል ማለት ነው፡፡ በዚህ ነገር እሺ ብሎ ለመጠቀምም ሆነ እምቢ ብሎ ለመጎዳት ለእያንዳዱ ሰው ነጻ ፈቃድ ተሰጥቶታል፡፡ ይህም *"ብትወዱኝስ ትእዛዜን ጠብቁ"* ባለው ቅዱስ ቃሉ ግልጽ ሆኖ ይታያል (ዮሐ14፡15)፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## ፫. ሕግጋተ እግዚአብሔር


*ውድ አንባብያን ህግ ለሰው ልጆች ያስፈለገበት ምክንያት ለምን ይመስላችሁል?*

*"ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው።" መዝ 118፡105*

**ሕግ** የሚለው ቃል የአለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት በቁሙ "የተወሰነ የተጻፈ ሥርዓት፣ ለማድረግ የሚያዝዝ፣ ከማድረግ የሚከለክል፣ አታድርጉ በማለት የሚከለክል" ብሎ ይፈታዋል፡፡ በዚህ ፍቺ መሰረት በእነዚህ በየፈርጁ የተለያየ አስገዳጅነት ባህርይ ባላቸው ሕግጋት መሠረትነት ላይ ተመርኩዞ የሚገዛ ወይም የሚስተዳድር አንድ አካል መኖሩን ያስታውሷል፡፡ ይህ ትእዛዝ ደግሞ በመናገር ወይም በጽሁፍ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ስለሆነም ሕግ ስንል የተጻፈውን ብቻ ሳይሆን ያልተጻፈውን ፡- በቃል በልማድ የሚሠራበትን ጭምር ያጠቃልላል፡፡ በዚህ ውስጥ በልማድ የሚሠራባቸው ያልናቸው፤ ሰው ከተፈጥሮ ባሕርዩ የተነሳ ማንም ሳያዝዘው የሚፈጽማቸውና የሚመራባቸው ሕግጋት ልቡና ናቸው፡፡

ለአፈጣጠሩ ስርዓትን አበጅቶ የፈጠረው እግዚአብሔር ከፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ከህግና ስርዓት ውጪ የሆነ አንድም እንኳን እንዲኖር አልፈቀደምና ለሁሉም እንደየወገኑ የሚመራበትና የሚኖርበትን ሕግና ስርዓትን ሰርቷል፡፡ ይህ ሕግና ስርዓት በሰው ልጅ ዘንድ በልቡና የተቀረጸ፣ በቃል የተነገረ ወይም የተጻፈ ሊሆን ይችላል፡፡ የሰው ልጅም በመልካም ምግባር መኖር ይችል ዘንድ እግዚአብሔር ህግጋትን ስጥቷል፡፡

ሕግጋት ጠቅለል ባለ አከፋፈል መንፈሳዊ ወይም ሕግጋተ እግዚአብሔር እና ዓለማዊ ሕግጋት በመባል ይታወቃሉ፡፡




**፫.፩. ኢ-ጽሕፋዊ ሕግ**

ኢ-ጽሑፋዊ ሕግ የሚባሉት በጽሑፍ ያልሰፈሩ ለሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጡ ተፈጥሮዊ ህጎች ናቸው፡፡ እነሱም ሕገ ልቡና እና ሕገ ሕሊና በመባል ይታወቃሉ፡፡

- **ሕገ ልቡና፡-** በሰው ልቡና የተጻፈ ሳያረጅ ሳያፈጅ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ የሚኖር ህግ ማለት ነው፡፡ ሮሜ 2፥14 ሐዋ 16፥14-15
- **ሕገ ሕሊና፡-** ከእግዚአብሔር የሚሰጥ፣ ሰዎች በሕሊና ምስክርነት የሚገዙበት ሕግ ነው፡፡ አንድ ነገር እንዲፈጸም ወይም እንዳይፈጸም አስቀድሞ ምርጫን የሚሰጥ ከተፈጸመ በኋላ ውጤቱ በጎ ከሆነ የሚያበረታታት፣ በአንፃሩ ደግሞ የተግባሩ ውጤት ክፉ ከሆነ መጸጸትን የሚያመጣ ህግ ነው፡፡ ሮሜ. 14፥23

**፫.፪. ጽሑፋዊ ሕግ**

ጽሑፋዊ ሕግ፡- የሚባሉት በጽሑፍ ሰፍረው የምናገኛቸው እግዚአብሔር አምላክ ለሰው ልጆች የሰጠው ሕጎች ናቸው፡፡ እነሱም በብሉይ ኪዳን (10ቱ ትዕዛዝ) እና በሐዲስ ኪዳን (6ቱ ቃላተ ወንጌል) በመባል ይታወቃሉ፡፡

- **አሥርቱ ትዕዛዛት፡-** ከእግዚአብሔር አምላክ በቀጥታ በሙሴ አማካኝነት ለእስራኤላውያን የተሰጠ ህግ ነው፡፡ የተሰጣቸውም እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡ 3ኛው ፋሲካ ካከበሩ በ3ኛ ቀን በደብረ ሲና ሰፍረው ባሉበት ወቅት ነበር፡፡ ዘጸ 19፥1-4 ዘዳ 34፥28 4፥13 የሰው ልጅ በተሰጠው ተፈጥሮዊ ህግ(ሕገ-ልቦና) እየተመራ አምላኩ እግዚአብሔርን ማምለክ ስላልቻለ እግዚአብሔር አምላክ ጽሑፋዊ ህግ ለሰው ልጆች ሰጠ፡፡ ዘጸ 20፥3-17 ዘዳ 5፥5-21
- **ስድስቱ ሕግጋተ ወንጌል**፡- ጌታችን በሐዲስ ኪዳን ለሰው ልጆች ይመሩበት ዘንድ በቃሉ ያስቀመጠልን ሕጎች ሲሆኑ የ10ቱ ትዕዛዛት ማፅኛ ናቸው፡፡ ማቴ 5፥25-45

***መልመጃ አንድ***

*ትዕዛዝ ፩ አዛምዱ*

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| ፩. ሕግ | ሀ. ዘጸ. 20፥3 |
| ፪. ጽሑፋዊ ሕግ | ለ. ጽሑፋዊ ኢ-ጽሑፋዊ |
| ፫. 10ቱ ሕግጋት | ሐ. ዘፀ. 20፥10 |

፮. 6ቱ ሕግጋተ ወንጌል መ. ማቴ. 25

ሠ. ማቴ. 5፥40

ረ. ፍቅረ እግዚአብሔር ፍቅረ ቢጽ

ሰ. ነ0ቱ ሕግጋት 6ቱ ሕግጋተ ወንጌል

*ትዕዛዝ ፪ ባዶ ቦታውን ሙሉ*

፩. ____________________ እና ___________________ የሰው ልጅ ስነ-ምግባር መገለጫዎች ናቸው ፡፡

፪. ከክርስቶስ ለሰው ልጅ በቀጥታ የተሰጡና ነ0ቱ ትዕዛዛት የሚያጠናክሩ ናቸው ፡፡

፫. ህግጋት ______________________________እና ___________________________ ተብለው ይከፈላሉ ፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ፬. አሥርቱ ትዕዛዛት

በነጣ ጠባይ በልቦናዊ ህግ እየተመራ ለዘለዓለም ሥላሴን በማምለክ ይዋብ ዘንድ የተፈጠረው የሰው ልጅ ህግን በመጣሱ ለፈቃደ ስጋው ተገዢ ለመሆን በቃ፡፡ ከሰብዓዊ ገዢነት ወደ ተገዢነት ተሸጋገረ፡፡ የልቦና ህግ የማይጠፋ ዘላለማዊ አምልካዊ ስጦታ ቢሆንም አጥርቶ እንዳያይ የኃጢአት ጉም ሸፈነው(ጋረደው)፡፡ ከመልአካዊ ማንነቱ ይልቅ እንስሳዊ ስብዕናን በመላበስ የሰው ልጅ ሊፈጽመው በማይገባ ክፉ ምግባር እና ኃጢአት ወደቀ፡፡ በዚህም በተፈጥሮአዊ ህግ እየተመራ ልዑል እግዚአብሔርን ማመልክ እንደ ፈቃዱም መሄድ ሲሳነው፤ ፈጥሮ የማይረሳ፣ የፍጥረቱ ነገር የሚገደው እግዚአብሔር ተመልክቶ ቸር አምላክ ነውና በቅዱስ እጆቹ የተጻፈ ዘመን ተሻጋሪ ህግን በሙሴ አማካኝት ለሰው ልጅ ሰጠ፡፡ በሲና ተራራ ላይ ነብዩ ሙሴ 40 ቀን 40 ሌሊት ከጾመ በኃላ በሁለት ጽላቶች ላይ የተጻፈ ህግን ተቀበለ፡፡ ይህ የጽሑፍ ህግ አስርቱ ትዕዛዛት በመባል ይጠራል፡፡ የአስርቱ ትዕዛዛት ዝርዝር እንደሚከተለው ይቀርባል፡-

**፩.** ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ፡፡ ዘጸ 20፥2

**፪.** የእግዚአብሔር አምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፡፡ ዘጸ 20፥7

**፫.** የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ፡፡ ዘጸ 20፥3-11

**፬.** አባትና እናትህን አክብር ዕድሜህ በምድር ላይ ይረዝም ዘንድ፡፡ ዘጸ 20፥12

**፭.** አትግደል፡፡ ዘጸ 20፥13

**፮.** አታመንዝር፡፡ ዘጸ 20፥14

**፯.** አትስረቅ፡፡ ዘጸ 20፥15

**፰.** ባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፡፡ ዘጸ 20፥16

**፱.** የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፡፡ ዘጸ 20፥17

**፲.** ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ፡፡ ዘሌ 19፥18

በሙሴ አማካኝነት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠው ህግ (ትዕዛዝ) የብሉይ ኪዳን እና የሐዲስ ኪዳን መሰረት ነው፡፡ ዮሐ 14፤ 15 *"ሕግን ብትጠብቁ፣ ብትፈጽሙትም ሕዝቤ ትሆናላችሁ እኔም አምላካችሁ እሆናለሁ።"* ዘጸ 19፤8-24፤ ዕብ 18፤22 በሐዲስ ኪዳንም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አላቸው፡፡ ማቴ 5፤17 19፤15

## ፬.፩ የአሥርቱ ትዕዛዛት ዓላማ

አስርቱ ትዕዛዛት የተሰጡበት ሦስት መሠረታዊ ዓላማዎች እንደሚከተሉት ይቀርባል፡-

፩. ከግብፅ ባርነት ስላወጣቸው ውለታውን እንዲያስቡ

፪. መንፈሳዊ አካሄዳቸውን እንዲመረምሩ፣ ምን መሆን እንዳለበት እንዲያውቁ

፫. ከመናፍቃን፣ ከከሃዲያን ትምህርት እንዲጠበቁ (ከእግዚአብሔር ጋር መንፈሳዊ ትስስር እንዲኖራቸው) ሲባል አስርቱ ትዕዛዛት ሊሰጡ ችለዋል፡፡

## ፬.፪ የአሥርቱ ትዕዛዛት አከፋፈል

### ፬.፪.፩ ከፍቅር አንጻር ሲከፈሉ

አሥርቱ ትዕዛዛት **በፍቅር** አከፋፈል ሲከፈሉ **በሁለት** ይከፈላሉ፡፡ ማቴ 22፤34-41 ይህም እግዚአብሔርን ስለመውደድ የምንፈፅመውና ሰውን (ባልንጀራን) ስለመውደድ የምንፈፅመው ሕግጋት ናቸው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈላቸው መልዕክቱ ላይ «እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፡፡ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሚታልና፡፡» ሮሜ 13፤8 በማለት ተናግሯል፡፡ በዚህ መሰረት አስርቱ ትዕዛዛት በፍቅር አከፋፈል ሲከፈሉ፡-

**፩.ፍቅረ እግዚአብሔር** - ከ1ኛ- 3ኛ ያሉት ትዕዛዛት ሲሆኑ እግዚአብሔርን የሚመለከቱና እርሱን ስለመውደድ የምንፈፅማቸው ትዕዛዛት ናቸው፡፡

**፪.ፍቅረ ቢፅ** - ከ4ኛ- 10ኛ ያሉት ትዕዛዛት ሲሆኑ ባልንጀራን የሚመለከቱ እና ባልንጀራን ስለመውደድ የምንፈጽማቸው ትዕዛዛት ናቸው፡፡

### ፬.፪.፪ ከተነገሩበት አንጻር በሁለት ይከፈላሉ

**፩.** በአሉታ የተነገሩ ትዕዛዛት (አታድርግ) እና
**፪.** በአወንታ የተነገሩ ትዕዛዛት (አድርግ) የሚሉ ናቸው፡፡

### ፬.፪.፫ ከአፈጻጸማቸው አንጻር ሲታዩ በሦስት ይከፈላሉ፡፡

**፩.** በሐልዮ (በማሰብ) ፡- በማሰብ የሚፈፀሙ ትዕዛዛት፡፡ ለምሳሌ ፡- የባልንጀራህን ቤት አትመኝ...
**፪.** በነቢብ (በመናገር) ፡- በመናገር የሚተገበሩ ትዕዛዛት፡፡ ለምሳሌ ፡- ትዕዛዝ ሁለት እና ትዕዛዝ ስምንት ናቸው፡፡
**፫.** በገቢር (በመሥራት)፡- በሀሳብ የተጠነሰሰውን በተግባር የሚገለጥበት፤ በመስራት የሚፈጸሙ ትዕዛዛት ይባላሉ፡፡ ለምሳሌ ፡- አታመንዝር፣ አትግደል፣ አትስረቅ ወ.ዘ.ተ ናቸው፡፡

## ፬.፫. የአስርቱ ትዕዛዛት ዝርዝር ጥናት

*ውድ ተማሪዎች ባለፉት ምዕራፎች ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና አስርቱ ትዕዛዛትን ጠቅለል ባለ መልኩ እግዚአብሔር በፈቀደ ለመመልከት ሞክረናል፡፡ በዚህ ምዕራፍ አስርቱ ትዕዛዛትን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡ ትምህርታችንን ከመጀመራችን በፊት ይህንን ጥያቄ እንድትሞክሩት እንጋብዛለን፡፡ ከእግዚአብሔር ውጪ ሌላ አምላክ እንዳናመልክ የተከለከለው ለምን ይመስላችኋል?*

## ፩.፫.፩ ትዕዛዝ አንድ - *"ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁንልህ" ዘጸ 20፥2*

የሁሉ አስገኝ፣ የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ፈጣሪ መጋቢ የለም፡፡ መዝ 99፥3 ዘፍ 1፥1 ዮሐ 1፥3 14፥15 ፍጥረታቱን ፈጥሮ የሚመግብ ልዑል እግዚአብሔር የፈጥረቱ ነገር የሚገደው ደግ አባት ነው፡፡ የፈጠራቸው ፈጥረታቱ የእሱን አምላክነት ተረድተው በነጻነት እንዲያመልኩት የፈቀደ አምላክ ነው፡፡ የሃይማኖት ዝንባሌ ያለው የሰው ልጅ ያለ ሃይማኖት የኖርበት ጊዜ የለም፡፡ ይህ ማለት እውነተኛውን ፈጣሪ በማምለክም ሆነ በሌሎች ነገሮች በማምለክ ከሃይማኖት ዝንባሌ ወጪ ሆኖ አያወቅም፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ የእሱን (እግዚአብሔር) አምላክነት ወደጎን በማድርግ የእግዚአብሔር የእጁ ስራዎች በሆኑ ፍጥረታት አልያም በእጁ ባለዘባቸው ጣኦታት ሲያመልክ ኖሯል፡፡ እየኖረም ይገኛል፡፡ ይህ የከንቱነት ህይወት የወለደው የጣኦት አምልኮ ነው፡፡ አንድ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ያለ እርሱ መጋቢ የለም፡፡ ዘፍ 1፥29 መዝ 135፥25 146፥7-11 ማቴ 6፥25-33

### ይህንን ትዕዛዝ የሚክዱ ሰዎች

- የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር የተባለውን ትዕዛዝ ይክዳሉ፡፡
- ከቤተ-ክርስቲያኑ ውጪ ይሆናሉ፡፡
- ተስፋ ቢስ ሁሉ የጨለመባቸው ሆነው ይገኛሉ፡፡
- ለመላእክትና እግዚአብሔር ላከበራቸው ሁሉ አክብሮትን አይሰጡም፡፡ ማቴ. 10፥41-42 2ኛ ቆሮ 9፥13

## ፩. ሌሎች አማልክት የተባሉ (የባዕድ አምልኮ ዓይነቶች)

### ሀ. ገንዘብ ማምለክ

የሰው ልጅ በምድራዊ ኑሮ ከሚጠቀምባቸው አሰፈላጊ ነገሮች አንዱ ገንዘብ ነው፡፡ የገንዘብን አጠቃቀሙን ያልተረዱ ብዙ ሰዎች የተንበረከኩለትና የተገዙለት፤ በሰዎች ውስጥም የእግዚአብሔርን አምላክነት የሚቀናቀን ጣዖት ነው፡፡

> *"ለሁለት ጌታ መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፣ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፡፡. . . . . . . .ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም፡፡" ማቴ. 6፥24*

ገንዘብን ከእግዚአብሔር አስበልጦ መውደድ ጣዖትን ማምለክ ነው፡፡ ገንዘብን ለአምልኮ ጣዖት መፈጸሚያና ለኃጢአት አገልግሎት ማዋል ማለት ገንዘብ አምላክ ሆኖ እየተመለከ ነው ማለት ነው፡፡ ስለገንዘብ ብለው እግዚአብሔር አምላካቸውን የሚክዱ፣ ወንድማቸውን የሚገድሉ፣ እስከ ሞት ድረስም ራሳቸውን መሰዋዕት የሚያደርጉ ብዙ ናቸው፡፡

> *"ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፡፡" ማቴ 6፥19*

### ለ. መልካም ያደረጉልንን ማምለክ

ብዙዎች ውለታ የዋሉላቸውን ሰው ለማክበርና በሚገባው መጠን ከማፍቀር አልፈው ያመልኳቸዋል ወይም ፈፅመው ይገዙላቸዋል፡ ፡ ይህ ማለት ውለታ ለዋሉልን ሰዎች ሰንል ከሃይማኖታዊ ትዕዛዛት ወጪ በይሉኝታ የሚፈጽሙትን ስህተት ለማመልከት ነው፡፡ ሰው መልካም ነገር የሚያደርገው ስለሰማያዊ ዋጋ ብሎ እንጂ የሌሎች ገዢዎች ወይም በሰዎች ልቡና ጣዖት ለመሆን ብለን መሆን የለበትም፡፡

### ሐ. ታላላቅ ሰዎችን ማምለክ

*"ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፣ እነርሱ... ስለነፍሳችሁ ይተጋሉ፡፡"* ዕብ 13፥17 ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ታዘዙአቸው እንጂ በእግዚአብሔር ፈንታ አምልኳቸው ማለት አይደለም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ታላላቅ ለሚሏቸው ታዋቂ ሰዎች አቅላቸውን እስኪስቱ ድርሰ ይገዛሉ፡፡ ሐዋርያት አባቶቻችን *«ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል፡፡» በማለት እንደገለጹት ሰው ሁሉ ለፈጣሪ ሊገዛ ይገባል እንጂ ለባለጸጎች ወይም ለባለስልጣን በመገዛት የእግዚአብሔርን ዓላማ ወደ ጎን ማለት የለበትም፡፡ ሐዋ. 5፥29*

### መ. ራስን ማምለክ

ከጣዖት ሁሉ የበለጠውና አደገኛው ጣዖት ራስን ማምለክ ነው፡፡ ሰው ከሥጋዊ ፍላጐቱ ማየል የተነሳ ሁል ጊዜ ራሱን ከፍ ከፍ ማድረግ ይፈልጋል፡፡ ሰው ከራሱ አልፎ ሌሎች እንዲያመልኩትና እንዲገዙለት ይፈልጋል፡፡ ሰውን ከእግዚአብሔር እንዲለይ ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል ዋነኛው ከምንም በላይ እራስ መከተል፣ በራስ ማስተዋል መደገፍ፣ ከእኔ በላይ ሰው የለም ብሎ

ማሰብና ራስን ማምለክ ናቸው፡፡ የመላዕክት አለቃ የነበረው ሣጥናኤል ክብሩን ያጣው ራሱን ከሁሉ በላይ ከፍ በማድረጉ ነው፡፡ ኢሳ. 14፣13-14

***ሠ. ዓለምንና የዓለምን ፍላጎት ማምለክ፡-*** የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንመለከት፡-

- *"ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጠላት እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖል" ያዕ. 4፣4*
- *"ከእግዚብሔር የተወለደው ሁለ ዓለምን ያሸንፋልና፣ ዓለም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው፡፡" 1ኛ ዮሐ. 2፣15-17*
- *"ዴማስ ይህንን የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛል፡፡" 2ኛ ጢሞ 4፣10*

አንዳንድ ሰዎች ከአፈር መፈጠራቸውንና ወደ አፈር መመለሳቸውን በመዘነጋት ውበታቸውን ያመልካሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ትኩረታቸው መብልና መጠጥ ነው፡፡ "ሆዳቸው አምላካቸው ነው፡፡ ክብራቸው ነውራቸው, ሃሳባቸው ምድራዊ ነው፡፡" እንዳለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ፊል. 3፤19

እስራኤላውያን በአንድ ወቅት ስለሥጋ፣ ዓሣ፣ ዱባ፣ ቀይ ሽንኩርት አልቅሰው ነበር፡፡ ዘኁ 11፤4-5 ኤሳው በኩርናውን ከነበረከቱ በምስር ወጥ ለውጧል፡፡ ዘፍ. 25፤29 ሰው የሚኖርበት ዓላማ ሲያረዳ ሲቀር ለምድራዊ ሀሳቦች ተገዢ ይሆናል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰው በራሱ መንግድ ሲጓዝ ምን እንደሚገጠመው የሚያስተመሩ ብዙ ታሪኮች ይገኛሉ፡፡ ለአብነት አዳምና ሔዋን ማንሳት ይቻላል፡፡ ዘፍ 3፣6 ቅዱሳን ለጣዖት ከመንበርከክ ይልቅ ሰማዕትነት ይመርጡ ነበር፡፡ የዘመኑ ወጣት ግን በተቃራኒው ለጣዖት ሲንበረከኩ ይታያል፡፡ ሥልጣንን፣ ማዕረግን፣ ክብርን፣ የተለያዩ ንብረቶችን የሚያመልኩ እንዳሉ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

***ረ. ሰይጣንንና አጋንንትን ማምለክ***

***መጽሐፍ ቅዱስ፡-*** ከአምልኮተ እግዚአብሔር ውጪ የሆኑትን አሕዛብ ብሎ ሲጠራቸው እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን ደግሞ ሕዝብ ይላቸዋል፡፡ "የአሕዛብ አማልክት ሁሉ አጋንንት ናቸው፡፡" መዝ 95፣5 በተጨማሪ እነዚህ ጥቅሶች ተመልከት፡- ዘዳ 18፣9 ሐዋ 16፣1-18 ሐዋ 89፣25

**፪. የተቀረፀውን ምስል ለአንተ አታድርግ**

**የተቀረፀ ምስል**፡- የተቀረፀ ምስል የሚባሉት ከድንጋይ፣ ከእንጨት፣ ከተለያዩ ቅርፃ ቅርጾች በሰው እጅ የሚሰሩ ባለ ሶስት ጎን ቅርጾች ናቸው፡፡ የሰው ልጅ በተፈጥሮ የሃይኖማት ዝንባ እንዳለው ቅዱሳት መጽሐፍት ያወሳሉ፡፡ ታዲያ እውነተኛው ፈጣሪ እግዚአብሔርን በማምለክ ፈንታ የእግዚአብሔር የእጁ ስራ የሆኑትን ድንጋይ በማለዘብ፣ እንጨት በመጠረብ ለፈጣሪ የሚገባውን ክብር በእጁ ለሰራቸው ግዑዛን ሲሰጥ እንመለከታለን፡፡ ይህ የሰው ልጅ የኃጢያት ከፍታ የአእምሮን ድረቀት በማስከተሉ እንሳስት እንኳን ለማይፈጽሙትን እጅግ አስነዋሪ ድረጊቶች ተገዢ አደረገው፡፡ የአእምሮ ጠባዩን ጠብቆ ፈጣሪን በማምለክ እንዲዋብ ህግ ለሰጠ አሰፈለገ፡፡

አንዳንድ ሰዎች የኦርቶዶክሳዊት ቅድስት ተዋህዶ ቤ/ክ አስተምሮ ባለመረዳት ለቅዱሳን፣ለታቦት እና ሥዕላት የምንሰግደውን የፀጋ(አክብሮት) ስግደት እንደ ጣኦት አምልኮ የሚመለከቱ አሉ፡፡ ቅድስት ቤ/ክ እግዚአብሔር ላከበራቸው ቅዱሳን፣ ለማደራወ ለታቦቱ እንድንሰግድ የምታስተምርን የአምልኮ ስግደት ሳይሆን አክብሩት ስግደት ነው፡፡ ባለቤቱ ያከበራቸውን እኛም እናከብራቸዋለን፡፡ ለቅዱሳን የምንሰግደው የጸጋ ስግደት ስለምንወዳቸው፣ ፍቅራቸውን፣,, ተጋድሎአቸውን እያሰብን ነው፡፡

## ***፩.፫.፪ ትዕዛዝ ፪***

*"የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ አምላክሕ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራው ከበደል አያነፃውምና" ዘጸ 20፣7*

***ሀ.የእግዚአብሔር ስም፡-***

**፩.ቅዱስ ነው**

የእግዚአብሔር ስም እንደ ሌሎች ስሞች አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ስም ግርማ ያለው፣ በእምነት የጠራውንም ሆነ የሰማውን የሚባርክ፣ ለፍጥረታት ተስፋን የያዘ ባለመድኃኒት ስም ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ስም አባቶቻችን ሲጠሩም ሆነ ሲጽፉ ታላቅ ጥንቃቄ እና ክብርን ይሰጣሉ፡፡ በሰይፈ ሥላሴ ዘረቡዕ ተአምር ላይ አንድ ጸሐፊ ለሥላሴ ስም ታላቅ ክብርን በመስጠት በወርቅ ቀለም በመጻፉ መንግስተ ሰማያትን ለመውረስ እንደ በቃ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ እመቤታችን ስለ ቅዱስ ስሙ በሉቃ ወንጌል 1፤ 49 ላይ መስከራለች "ብርቱ የሆነ እርሱ ታላቅ ሥራ ለእኔ አድርጓልና ስሙም ቅዱስ ነው"፡፡ መዝሙኛረው ቅዱስ ዳዊትም "ስሙ

የተቀደሰ እና የተፈራ ነው፡፡" መዝ 110፤9 በማለት ይገልጻል፡፡ በዮሐንስ ራዕይ ዩሐ.ራ ዕ 4፤8-10 "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረና ሁሉን የሚገዛ ጌታ..." ተብሎ ተግጽዋል፡፡

**፪. ታላቅ እና ምስጉን ነው**

"ስምህ በምድር ሁሉ እጅግ የተመሰገነ ምስጋናህም ከሰሞች ላይ ከፍ ብሏልና" በማለት ነብየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት በመዝ 8፤ 1-9 ላይ ይገልጻል፡፡ ነብዩ ኢሳይያስም የስሙን ምስጉንነት ሲያስረዳን "ስሙ ድነቅ መካር ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል፡፡" ኢሳ 9፤6 በማለት ይገላጻል፡፡
የእግዚአብሔር ስም ቅዱስ መሆኑን በነቢያቱ አንደበት ከተመሰከሩት ውስጥ ት.ኤር 10፥6 "እንዳተ ያለ የለም አንተ ታላቅ ነህ ስምህም በኃያል ታላቅ ነው፡፡" 2ኛ ሳሙ 7፤26 "ስምህ ለዘላለም ታላቅ ይሁን" በማለት ቅዱሳት መጽሐፍት ይመሰክራሉ፡፡
ከላይ የተጠቀሰው ተግባራዊ ማስረጃ ወይም መገለጫ የሚሆኑ፡-

**፫. የእግዚአብሔር ስም ድንቅ ተዓምራትን የደርጋል**

የሐዋ.ሥራ. 3፥6 ብርና ወርቅ የለኝም፡፡ ያለኝን ግን አሰጥሃለው፡፡ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነስና ተመላለስ" ብሎ ቅዱስ ጴጥሮስ ሽባውን በእግዚአብሔር ስም ፈውሶታል፡፡

**፬. የእግዚአብሔር ስም ለአጋንንት አስደንጋጭ ነው**

በሉቃስ ወንጌል ላይ ተምዝግቦ የምናገኘው ታሪክ ሐዋርያት አባቶቻችን አጋንንት በጌታ ስም ስለ ተገዙላቸው ደስ ብሏቸው "ጌታ ሆይ በስምህ አጋንንት ተገዝተውልናል፡፡" 10፥17 በማለት ተናግረዋል፡፡ አጋንንትን የማውጣት ስልጣን እንደሰጣቸው በማርቆስ 16፤ 17 ያረጋግጣል "ያመኑት እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፡፡ በስሜ አጋንንት ያወጣሉ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፡፡"

ቅዱስ ጳውሎስም በሐዋ.ሥራ 16፥18 "ከእርሷ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝዤሃለው አለው፡፡ በዚያም ሰዓት ወጣ፡፡" በማለት አጋንንትን በስሙ አውጥቶዋል፡፡

## ለ. የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ

*ውድ ተማሪዎች ከንቱ ማለት ምን ማለት ይመስላችሁል?*
ከንቱ ማለት በእግዚአብሔር የተናቀ የማይጠቅም የማይረባ ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ስም በሁሉ ቦታ በማንኛውም ጊዜ የማይጠራ የተከበረ ባለግርማ ስም ሰለሆን ለማይገባ ነገር የእግዚአብሔር ስም መጠራት በከንቱ መጥራት ይባላል፡፡ የእግዚአብሔር ስም መጥራት ከንቱ ከሚያደርጉት ውስጥ፡-

**፩ በሐሰት መማል**

መሐላ ማለት አንድን ነገር ምስክር አድርጎ መጥራት ሲሆን ባላየነውና ባልሰማነው ነገር ሰምተናል ብለን የተለያዩ ጥቅሞችን ለማግኘት አለያም ከችግር ለማምለጥ ብለን እንዲታመንልን የእግዚአብሔርን ስም ማንሳት ወይም መጥራት በሐሰት መማል ይባላል፡፡ ት.ዘካ 5፥4 «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ወደሚሰርቀው ቤት በሐሰትም በስሜ ወደሚምለው ቤት ይገባል፡፡ በቤቱም ውስጥ ይኖራል እርሱንም እንጨቱንም ድንጋዩንም ይበላል፡፡»

በብሉይ ኪዳን እስራኤላዊያን በእግዚአብሔር ስም በእውነት እንዲምሉ ተፈቅዶ ነበር፡፡ዘዳ 6፥13 ዘዳ 10፥20
**፪ በእግዚአብሔር ስም መራገም**

በክርስትና ህይወት ውስጥ ሁሉን ነገር ማሸነፈ የሚቻለው በፍቅር እንጂ በጥላቻ ማሸነፍ አይቻልም፡፡ መጥፎ ያደረጉብን ሰዎች እንኳን በኖሩ ከመርገም ይልቅ መመረቅ እንደሚገባን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ ሮሜ 12፥14 "የሚያሳድዱአችሁን መርቁ እንጂ አትርገሙ፡፡"

**፫ መጠቀስ በማይገባው ቦታ በማንሳት**

የእግዚአብሔርን ስም የልጆቻችው ስም በማድረግ ማውጣት የለብንም፡፡ ለምሳሌ አማኑኤል፣ ኤልሻዳይ፣ አንዱ አምላክ ...ወዘተ በማለት ማውጣት የለብንም፡፡ ሌላው በዘፈን ላይ የእግዚአብሔርን ስም ማንሳት፤ ከኃጢአት ሥራዎች ውስጥ ስለሚመደብ ማንሳት አይገባም፡፡ ገላ 5፥19
**፬ በእግዚአብሔር ላይ ማጉረምረም**

እግዚአብሔር አምላካችን በፍቅሩ ወረት የሌለበት አምላክ ነው፡፡ ለፍጥረቱ ያለውን ድንቅ ዓላማ እሱ ባወቀ በተለያዩ መንገዶች ይገልጣል፡፡ በእግዚአብሔር የሚያምን ሰው በህይወቱ ሚከሰቱ ማንኛውም ነገሮች ለበጎ እንደሆነ ማመን እንደሚገባው ቅዱሳት መጽሐፍት ያስተምራሉ፡፡ ስለዚህ በመከራ ውስጥ እንኳን ብንሆን በአውሎ እና በወጀብ መንግድ ያለው በእግዚአብሔር ማመን እና ምስጋና ማቅረብ ይገባል እንጂ ማማረረ አይገባም፡፡ ሕዝበ እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ ሲያጉረመርሙ እሳት ወርዶ ከሰፈሩ አንዱን ወገን በላቸው፡፡ ዘጸ 11፤1 ዘጸ 14፤1-38 ሕዝቡ በማመፁና በማጉረምረሙ ከንዓንን እንዳይወርሱ ተከለከሉ፣ የአርባ ቀን መንግድ የአርባ ዓመት መንገድ ሆነ፡፡

**፫ በእግዚአብሔር ስም በሐሰት መተንበይ**

በእግዚአብሔር ስም ሐሰተኛ ትንቢት መናገር የእግዚአብሔርን ስም ማቃለል ነው፡፡ ወደፊት የማይመጣውን ይመጣል በማለት የተለያየ ጥቅም ወይም ክብርን ሽተው የሚደደረጉ ናቸው፡፡ "እንዲህ ለሚያደርጉ ወየውላቸው" ይላል፡፡ ሕዝ 13፤1-23

**፬ በእግዚአብሔር ስም የተናገርነውን አለመፈፀም**

ብዙ ሰው የገባውን ቃል ያጥፋል ወይም ይረሳል፡፡ ስመ እግዚአብሔርን ጠርተን ለመፈጸም ቃል የገባነው ካለ መፈጸም ይኖርብናል፡፡ ስዕለት ተስለን ቃላችንን ካልፈጸምን፣ ለሰውም እናደርጋለን ብለን ቃል ገብተን ካልፈጸምን የእግዚብሔርን ስም በሐሰት ጠርተናል ማለት ነው፡፡ "እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ ይናገራሉ በሥራችው ግን ይክዱታል" ቲቶ 1፤16

## ሐ. የእግዚአብሔር ስም የምንጠራው በምን ጊዜ ነው

*ውድ አንባብያን የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት እንደማይገባ ከዚህ ቀደመ በነበረው ርዕስ ተመልክተናል፡፡ በዚህ ርዕስ ስር የእግዚአብሔርን ስም መጥራት የሚገባን ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ጉዳዮች እንደሆነ እንመለከታለን፡፡*

- በጸሎት ጊዜ ኢሳ 2፤32, ዩሐ 14፤14
- በአምልኮ ጊዜ መዝ 134፤3, ተ.ሚል 1፤4
- በሠላምታ ጊዜ 1ጴጥ 1፤1-12, ሮሜ 1፤9
- በቡራኬ (በምርቃት) ጊዜ ዘኁ 6፤23 2ቆሮ 13፡1

የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ለሚጠራ ሰሙን መጥራቱ ከበደል አያነፃውም፡፡ በወንጌል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያን ጊዜ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚሉኝ ሁሉ አይድኑም፣ ጌታ ሆይ በስምህ አጋንንትን አላወጣንምን? የሚሉትን ከቶ አላውቃችሁም እላቸዋለው፡፡ በማለት ተናግሯል፡፡ በተጨማሪ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመለከቱ፡-

ሕዝ 39፣25 "እግዚአብሔር ስለ ቅዱስ ስሙ ይቀናል፡፡" ዘካ 5፤3፣ ሚል 2፣2 "ስለስሜ ክብርን ትሰጡ ዘንድ ባትሰሙ እርግማንን እሰድባቹኃለው፡፡"

## ፬.፫.፫ ትዕዛዝ ፫ *"የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ፡፡*

*ውድ አንባብያን ይህ ትዕዛዝ አስርቱ ትዕዛዛት በፍቅር አከፋፈል ሲከፈል የፍቅር እግዚአብሔር የመጨረሻ ትዕዛዝ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡*

"ስድስተ ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ ሰባተኛው ቀን ግን እግዚአብሔር አምላክህ ሰንበት ነው፡፡ ...ሁሉን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፏልና ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበት ቀንን ባርኳታል ቀድሷታልም" ዘጸ 20፣10-11

ሰንበት የመንግስተ ሰማያት ምሳሌ ነች፡፡ በመንግስተ ሰማያት ጽድቃን ለዘላለም በምስጋና እረፍት ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ድካም ጠፍቶ ዘላለማዊ እረፍት ይነግሳል፡፡ ሰንበትም የመንግስተ ሰማያት ምሳሌ የሆነችው የሰው ልጅ ድካም በሚያመጡ ስራዎች ለስድስት ቀናት ተውጥሮ በመንፈሳዊ ስራ እና ምስጋና የሚያርፍባት በመሆኗ ነው፡፡ ትዕዛዙ ያስፈለገበት ዋንኛው ምክንያት ሰው በባህሪው ደካማ ስለሆነ ነው፡፡ ሰንበትን በማክበራችን በነፍስም በስጋም ተጠቃሚዎች ነን፡፡ ይህም፡-

***በነፍስ*** ***፡-*** ትዕዛዙን በመጠበቃችን በረድኤቱ ይጠብቀናል፣ ጸጋውን ያጎናፅፈናል፡፡

***በሥጋ*** ፡- ሰው በስጋው ተገቢውን እረፍት ካላገኘ ተገቢውን ውጤት አያመጣም፡፡ በተለይም ለጭንቀት እንዲሁም ለአዕምሮ መወጠር በሽታ የተጋለጠ ይሆናል፡፡

*ውድ አንባብያን መጽሐፍ ቅዱስ እንኳን በአርኢያ ሥላሴ የተፈጠርው የሰው ልጅ ይቅርና ግዑዟ ምድርም ማርፍ እንዳለባት ይገልጻል፡፡ ዘጸ 23፤10 "6 ዓመት ዝራ በሰባተኛው ግን ተዋት አሳርፋትም"*

### ፩. የብሉይ እና የሐዲስ ኪዳን ሰንበት ያላቸው ቁርኝነት (ተያያዥነት)

የብሉይ ኪዳን ስንበት ቀዳሚት ስንበት ወይም ሰንበተ አይሁድ ትባላለች፡፡ አይሁድ በቀዳሚት ሰንበት እረፍተ ሥጋ በማድረግ ያከብሩ ነበር፡፡ የሐዲስ ኪዳን ሰንበት ሰንበተ ክርስቲያን ዕለተ እሑድ ናት፡፡ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ለ5500 ዘመን በሲዖል ተዘፍቀው የነበሩ አዳም እና ልጆቹ በዕለተ እሁድ ለዘለዓለም አርፈው በደስታ ይኖሩ ዘንድ ጌታችን ሞትን ድል ነስቶ በትንሣኤው ትንሳኤያችንን ባጎናጸፈን ድል መሠረት ነው፡፡ በሰንበተ ክርስቲያን በዕለት እሁድ ድኅነተ ነፍስ ያገኘንበት የጌታን የቸርነት ስራ እናስብበታለን፡፡

ዘጸ 7፥15 "አንተ የግብፅ ባርያ እንደነበርክ አስብ እግዚአብሔር ከዚያ አወጣህ ስለዚህ የሰንበትን ቀን ትጠብቅ ዘንድ አስብ፡፡" ይህም ምሳሌ ነው ግብጽ - የሲዖል የፈርዖን ግዞት - የአጋንት አገዛዝ ነፃ መውጣት - ክርስቶስ በገለጠው ምስጢረ ትንሳኤ ነው፡፡

### ፪. እለተ እሑድን የምናከብርበት ምክንያት፡-

፩. እግዚአብሔር ፍጥረታት አሐዱ ብሎ መፈጠር የተጀመረበት ቀን ስለሆነ ዘፍ 1፥1

፪. ጌታ የተነሳበት እና እረፍታችን የተረጋገጠበት ዕለት ስለሆነ ዩሐ 20፥1-14

፫. መንፈስ ቅዱስ የወረደበት ዕለት በመሆኑ የሐ.ሥራ 2፥14

### ፫. ሰንበት ሁለት ነገሮችን ያስታውሰናል

፩. ሰው በኃጥያት ከመውደቁ በፊት ከአምላኩ ጋር የነበረውን ግንኙነት

፪. በጌታችን አዳኝነት የተቤዠውን የነፍስ እረፍት -- ዕብ፡- 4፥1-10


### ፬. ሰንበትን እንዴት እናክብር

የሰንበተ ቀን ከሥጋ ፈቃድ በመከልከል፣ ባልተከፈለ ልቡና፣ በተሰቀለ ሕሊና እግዚአብሔርን የምናመልክበት ቀን መሆኑን አውቀን በቤ/ክ በመገኘት በማህሌቱ፣ በሰዓታቱ በመገኘት፣ ኪዳንን በማድረስ፣ ቅዳሴን በመሳተፍ፣ ጸበሉን በመጠጣት፣ እረፍት የሆነ ቃሉን በመማር፣ ምስጋናን በማድረስ ቀኑን አክብረን መዋል ይገባል፡፡ በተጨማሪም በማቴ 12፥12 በሰንበት መልካም ነገር ማድረግ ተፈቅዷል ብሎ ጌታ እንዳዘዘ የተራቡን በማብላት፣ የተጠሙን በማጠጣት፣ የታረዙን በማልበስ፣ የተቸገሩትን በመርዳት ያዘኑትን በማረጋጋት ሰንበትን ማክበር ይገባናል፡፡

*ውድ አንባብያን ጌታችን በዳግም ምጽዐቱ ጊዜ የሚጠይቀን ነገር ቢኖር ለተቸገሩ ወንገኖቻችን ያደረግነው መልካም ስራ በመሆኑ ለመልካም ስራ ልንተጋ ይገባል፡፡ ማቴ፡- 25፥35*

## ፩.፫.፭. ትዕዛዝ ፭ *"እናት እና አባትህን አክብር"*

"እናት እና አባትህን አክብር እግዚአብሔር አምላክህን በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም" ዘጸ፡- 20፥12፣ ማቴ፡- 19፥18፣ ኤፌ፡- 6፥4 ከአስርቱ ትዕዛዝት መካከል የፍቅረ ቢጽ መጀመሪያ ትዕዛዝ የሆነው በአራተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው "እናትና አባት አክብር" የሚለው ትዕዛዝ ነው፡፡ እናትና አባት የምንላቸው የወለዱ ወላጆቻችን ብቻ ሳይሆኑ እንደ እናት እና አባት በሁለተናዊ ዕድገታች ላይ የእራሳቸው በጎ አስተዎጾ የሚደረጉ ሁሉ ናቸው፡፡ ለአብነት የሚከተለው እንመልከት፡-




| | |
|---|---|
| ፩. ወላጆቻችን ዕብ፡- 12፥9 | ፩. የንስሐ አባት |
| ፪. የትውልድ አባት ዮሐ፡- 4፥12 | ፪. ካህናት |
| ፫. አሳዳጊ (ሞግዚት) 1ቆሮ፡- 4፥15 | ፫. የወንጌል ሰባኪ 1ቆሮ፡- 4፥15 |

## ፩. አክብር

ማክበር ማለት መውደድ፣ መታዘዝ፣ መርዳት፣አለማቃለል ማለት ነው፡፡ ፍጥረታት በኑሮ ተከባብሮ መኖር መላመድ ይገባቸውል፡፡ ዘሌ፡- 19፤3 ቆላሲስ፡- 3፤20 ዘዳ፡- 27፤16

ለወላጆቻችሁ ታዘዙ ሲል የሚያመለክተን፦

፩. ምክራቸውን መስማት ምሳ፡- 1፤8, 1ሳሙ፡- 2፤25
፪. በተቸገሩ ጊዜ የሚያስፈልጋቸውን መስጠት ዘፍ፡- 4፤12
፫. በሌላቸው ጊዜ የሚረዱበትን መንገድ ማዘጋጀት ዮሐ፡- 19፤26
፬. በጠቅላላው ለወላጆች ብድራትን መመለስ

ይሁንና ወላጆቻችንም ሆነ ሌሎች ከእግዚአብሔር ጋር የሚያጣላ ትዕዛዝ ቢያዙን ከእግዚአብሔር ይልቅ እነርሱን መውደድ ማክበርም አይገባም፡፡ 1ሳሙ፡- 20፤31, ማቴ፡- 10፤35-37፣ ማቴ፡- 19፤22 ትዕዛዙን የሚጠብቅ ሰው በምድራዊ ሕይወቱ፡- በሕይወት፣ በጤና፣ በሰላም፣ ትዕዛዙን በመጠበቅ ይኖራል፡፡ ትዕዛዙን በመጠበቃችን የምናገኘው የድል አክሊል መንግስተ ሰማያትና የዘላለም ሕይወት፡፡

ልጆች ወላጆችን ማክበር እንደሚገባ ሁሉ ወላጆችም በጌታ ምክር ተግሳፅ እንዲያሳድጉ እንጂ በከንቱ እንዳያበሳጩአቸው ትዕዛዙ ያስረዳል፡፡ ኤፌ 6፤4 ቆላ 3፤21 የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማ ልጅ እናቱን ያሳርፋታል፡፡ ባሮቹም ለእራሱ እንዲገዙለት እራሱን ለወለደው ለአባቱ ይገዛል፡፡ ሲራክ 3፤9 "የአባት ምርቃት የልጅ ቤት ያድናል፣ የእናት እርግማን ግን መሠረት ይነቅላል፡፡"

## *፬.፫.፫ ትዕዛዝ ፮ "አትግደል" ዘጸ. 20፤13*

*ውድ አንባብያን በአምስተኛ ደረጃ ላይ የምናገኘው ትዕዛዝ አትግድል የሚለውን ነው፡፡ ሕይወት ማንም ሊያዝባት፣ እንደፈለገውም ሊያደርጋት የማይችልባት ድንቅ የአምላክ ንብረት ናት፡፡ ማንኛውም ሰው በእርሱ ላይ እንኳ ስልጣን የለው፡፡ ምክንያቱም ህይወት የእርሱ አይደለችምና፡፡*

**መግደል**፡- ማለት በተለያዩ መንገድ ተጠቅሞ የሰው ሕይወት እንዲያልፍ ማድረግ ነው፡፡ ማቴ 15፤19 ማር 7፤22 ገላ 5፤16 በተጨማሪም አንድን ሰውን ለሞት የሚያበቁ ነገርን መፈጸም እንደ መግደል ይቆጠራል ይኸውም፡-

- በተለያዩ ሁኔታ (በቃላትና በመጠቆም) አጥፊውን መርዳት
- ሰው ሊድን የሚችልበትን መረጃ መከልከል
- በሽታንና ድካምን እያዩ ለሞት የሚያደርስ ስራ ማሰራት
- በስጋ ብቻ ሳይሆን በነፍሱ መከራ የሚያመጣበትን መንገድ መፍጠር
- ሰው እንዳይድን እንዳይለወጥ መሰናከል መሆን ማቴ. 18፤6
- ሰውን እንዳይሰራና እንዳይለማ አድርጎ ሞራልን መንካት መግደል ነው፡፡
- ሰውን ከአግዚአብሔር መለየት እንዲርቅ ማደረግ፡፡ ኃጥያት፣ ሞት, ሮሜ. 6፤23
- በሐሰት ትምህርት በዓለማዊ ስብከት ሰውን ከእግዚአብሔር መለየት ዮሐ. 8፤44
- ሰውን ማሰናከል ማቴ. 18፤6
- ወንድሙን የሚጠላ እርሱ ነፍሰ ገዳይ ነው፡፡ 1ዮሐ. 3፤15 መሞት እንደማንፈልግ ሁሉ ለሌላውም የሚሞትበትን መንገድ ማዘጋጀት አይገባም፡፡

- ራስን መግደል፤ በራሳችን ላይ ስልጣን የለንም ስልጣን ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ዘፍ. 5፤
- ጽንስን ማስወረድ እንዳይወለድ መከላከያ ማድረግ መግደል ነው፡፡

### አትግደል ሲል፡-

- የሰዎች ደም በከንቱ ፈሶ አይቀርም እግዚአብሔር የአቤልን ደም ድምፅ ጩኸት ሰምቶ እንደተበቀለው ዛሬም ብድራትን ይመላሳልና በቀል የእራሱ ነውና፡፡ ሮሜ. 12፤19 ዘፍ. 4፤9-15 ነገር ግን ሕግ አጥፊዎችን መቅጣት ለባለስልጣኖች ተፈቅዷል፡፡ ዘዳ. 21፤18-23 የሐ.ሥራ. 13፤6-12
- እንዲሁም ቅናአት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ጥላቻ ቁጣ እና የመሳሰሉት ወደመግደል የሚያደርሱ ነገሮች ወይም ምክንያት ናቸው፡፡ ማቴ. 5፤21-22

## ፩.፫.፯ ትዕዛዝ ፯ "አታመንዝር" ዘጸ 20፤14

*ውድ አንባብያን ሰው ወደ አመንዝራነት የሚገባው ለምን ይመስላችኋል? የአመንዝራነት መንስኤና ውጤቱስ ምን ይመስላችኋል?*

አታመንዝር የሚለው ትዕዛዝ የንፅህና ሕይወት ምን መምሰል እንዳለበት የሚመራ ትእዛዝ ነው፡፡ የክርስቲያኖች የጾታዊ ሕይወት ከአራማውያንና ከአሕዛብ የተለየ ቅዱስ መሆን እንደሚገባው የሚያስረዳን ትዕዛዝ ነው፡፡

ጋብቻ የባል እና የሚስት ሕብረት ወይም ጥምረት ነው፡፡ ይህንን ጥምረት የፈጠረው፤ ጋብቻን ለሰው ልጆች ባርኮ የሰጠ ልዑል እግዚአብሔር ነው፡፡ በልዑል እግዚአብሔር ፍቃድ የተመሰረተ ስለሆነ የጋብቻ ሕይወትን ሰው ሊለያየው አየገባም፡፡ ማቴ. 19፤3-5

አባታችን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ « ጋብቻ ትንሿ ቤተ-ክርስቲያን ናት» በማለት ይናገራል፡፡ በቅዱስ ጋብቻ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ልጆች ይፈሩበታል፡፡ ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ምዕመናን ልጆቿን ቃለ እግዚብሔርን በመመገብ፣ መንፈሳዊ ትጥቅን በማስታጠቅ፣ መንፈሳዊ የእናትነት ግዴታውን እንደምትውጣ ሁሉ እግዚአብሔር ባለበት ክርስቲያናዊ ጋብቻ የሚወለዱ ልጆችን በሃይማኖት የታነጹ በምግባር የጎለመሱ፣ ለሀገርም ለውገንም የሚበጁ መልካም ዜጎች እንዲሁኑ ወላጆች የወላጅነት ሚናቸውን ይወጣሉ፡፡

### ፩. የጋብቻ ዋና ዓላማ

የቅዱስ ጋብቻ ዋና ዓላማ ሶስት ሲሆኑ እነርሱም፡-

፩. **ዘርን ለመተካት ዘፍ. 1፤27-28 ፡-** እግዚአብሔር አምላካችን አዳምና ሔዋንን ፍጥሮ «ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሏት፡፡» በማለት ባርኳቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት የቅዱስ ጋብቻ ተቀዳሚ ዓላማ ዘር ለመተካት ነው፡፡

፪. **እርስ በእርስ እንዲረዳዱ ዘፍ. 2፤18፡-** አበው በምሳሌ «ከአንዱ ብርቱ ሁለት መዳኃኒቱ» እንዲሉ በቅዱስ ጋብቻ ባልና ሚስት በሁሉ ነገር ሰለሚረዳዱ ጋብቻ ከሚመሰረትባቸው ምክንያቶችን አንዱ ሆነ፡፡ በጋብቻ ህይወት ባልና ሚስት የሚገጥማቸውን ማንኛውም የህይወት ውጣ ውረድ በመረዳዳት የጋራ መፍተረሄን ይፈልጋሉ፡፡

፫. **በፍቶተ እንስሳዊ እንዳይቸገሩ 2ቆ.7፤8-9፡-** የሰው ልጅ ለፍቃደ ምንታዊ የተጋለጠ በመሆኑ በአንድ ሰው ውስጥ መላዕካዊ ባህሪይና እንስሳዊ ባህሪይ ይንጸባረቃል፡፡ ከእንስሳዊ ባህሪይ አንዱ ፍቶተ ስጋ በመሆኑ የሰው ልጅ ከዚህ ይጠበቅ ዘንድ ጋብቻን መመስረት አስፈለገ፡፡

ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፡፡ ሚስትም እንዲሁ ለባልዋ የሚገባው ታድረግ፡፡ ይህም ሚስት በገዛ ስጋዋ ላይ ስልጣን የላትም ፍቃዷ ለባሏ ነው እንጂ ባልም እንዲሁ በገዛ ስጋው ላይ ስልጣን የለውም ፍቃዱ የሚስቱ ነው እንጂ፡፡

1ኛ ቆሮ 7፤2-6 ሰይጣን እንዳይፈትናቸው ራሳቸውን መግዛት ይችሉ ዘንድ አብረው እንዲሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ባልና ሚስት በሕይወት እያሉ በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በቀር በሌላ መፋታት አይችሉም፡፡ አንዳቸው ከሞቱ ግን ማግባት ይችላሉ፡፡

### የአመንዝራ ሕይወት በ3 ይከፈላል

**ሀ. ዝሙት፡-** በተልካሻ እና በርካሽ ተግባር ሕይወቱን ሙሉ ለጨለማ ጉዞ ተገዝቶ በመተዳደሪያነት ስራዬ ብሎ የሚኖር ሰው፡፡ 1ኛቆሮ. 6፥12-20

**ለ. ሴሰኝነት፡-** እግዚአብሔር ባዘዘው በጋብቻ ተወስኖ መኖር የማይፈልግና እራስ ወዳድነት ስግብግብነት የሚያጠቃው ሰው መገለጫ ነው፡፡

**ሐ. አመንዝራነት፡-** ባል ሚስቱን ትቶ ወይም ሚስት ባሏን ትታ ወደሌላ መሄድ ይህ አመንዝራነት በስሕተት የሚፈፀም ሳይሆን አስቦ አስልቶ ጨለማን ለብሶ ሰው አየኝ አላየኝ ተብሎ የሚሰራ ኃጢያት ነው፡፡

### ፪. የአመንዝራነት መንስኤ

ከአመንዝራነት ለመጠበቅ መነሻውን ( ምንጩን) ማወቅ ይገባል፡፡ ለአምንዝራነት መንስኤ የሆኑ ብዙ ነገሮች ቢኖሩም በዋነኛነት የሚከተሉት መንስኤዎችን ይጠቀሳሉ፡-

፩. መጠጥ፣ የወሲብ ፊልም እና መፅሔት፣ አደንዛዥ ዕፅ፣ ጭፈራ...

፪. ምኞት፣ ጠግቦ ሙብላት፣ ልቅ የሆነ አለባበስ፣ ከፉ ጓደኛ ...

፫. መተሻሸት፤ መላፋት ወዘተ... ቅዱሱን ሰውነት እንዲረክስ የሚያደርጉ ምንጮች ናቸው፡፡

### ፫. የአመንዝራነት ፍፃሜው

- የአዕምሮ (የሞራል) ሞት
- የስራ ወኔ ማጣት
- የመንፈስ ሞት
- የሥነ ምግባር ሞት
- በሰው ዘንድ የተጠላና ረብ የሌለው መሆን

### ፫. አመንዝራነት በመንፈሳዊ ገጽታ

አመንዝራነት ባለን ነገር አለመርካት(አለማመስገን)፣ ዓላማ ቢስ መሆን፣ በአንድ አለመወሰን፣ ወረተኝነት፣ ስግብግብነት ወ.ዘ.ተ የሚያካትት ሲሆን በተጨማሪም የሰው ልጅ የሃይማኖት ድንግልናውን አጥቶ ከእግዚአብሔር ሌላ ወደ ጣዖት አምላኮ መሄድም አንዱ የአመንዝራነት ገጹ ነው፡፡ ማቴ. 12፥38

☞ ***ወድ ተማሪዎች አሁን ካለው እይታ አንጻር ግብረ ሰዶም በሀገራችን መስፋፋትን እንዴት ታዩታላችሁ ? እያስከተለ ያለውስ ጉዳት ? መፍትሔውስ ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?***

### ፬. ግብረ ሰዶም

የግብረ ሰዶም ኃጢአት ከዝሙት በበለጠ እጅግ የከፋ ኃጢአት ነው፡፡ እግዚአብሔር ከፈቀደው ወጪ ከተመሳሳይ ፆታ ጋር የሚደረግ የረከሰ ግንኙነት ሲሆን እንስሳት እንኳን የማይፈፅሙትን የሰው ልጅ በመፈጸም ከላሸቀ አእምሮ የሚወለድ ሰይጣናዊ ስራ ነው፡፡ ከላይ እንደ ተመለከትነው የሰው ልጆች እንዲበዙ የፈቀደ፣ ጋብቻን ባረኮ ለሰው ልጆች የሰጠ ልዑል እግዚአብሔር ነው፡፡ ለአዳም አንድ ሔዋን ሰጠ እንጂ ሌላ በጾታ የሚመስለው አጋር አላዘጋጀላትም፡፡ እግዚአብሔር ከፈቀደው የተቃሪኒ ጾታ ጋብቻ ውጪ ለፍቃደ ምንታዊ የተጋለጠው የሰው ልጅ በደመ ነፍስ ህያውያን ሆነው የሚኖሩ እንስሳት እንኳን የማይፈጽሙትን የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት በመፈጸም ለማይረባ አእምሮ ተላልፎ ተሰጠ፡፡ በዚህ ከፉ ግብር የሰዶም እና የጎመራ ሰዎች ከሰማይ እሳት ወረዶ በላቸው፡፡ በዘመናችን ግብረ ሰዶም እንደ ሰብዓዊ መብት ተድርጎ በምዕራብዊያን የሚቀርበው ሀሳብ ከክርስትና ትምህርት ፍጹም የወጣ ነው፡፡ ሰብዓዊ ማንነትን ነጥቆ ከእንሳት እንኳን የሚያሳንስ ግብርን ከሰብዓዊነት ጥያቄ ጋር መያያዙ ትውልዱ ወደ ጥፋት እያመራ መሆኑን ያሳያል፡፡

## ፬.፫.፯ ትዕዛዝ ፯ "አትስረቅ" ዘጸ 20፥15

ሰው ሁሉ ያልደከመበትን ንብረት እንዳይፈልግ፣ የራሱን ብቻ ሠርቶ እንዲጠቀም፣ ጉልበተኛው አቅመ ደካማውን እንዳያጠቃው፣ ሁሉ ተስማምቶ እና ተቻችሎ እንዲኖር የተሰጠ ሕግ ነው፡፡ ይህ ትዕዛዝ የሚያመለክተን ነገረ ቢኖር የሰው ልጅ በላቡ ጥሮ ግሮ ያገኘውን ዋጋ ሌላው ያልደከመበት በጉልበት መቀማት እንደሌለበት ነው፡፡

ውድ አንባብያን እግዚአብሔር አምላክ ሰው እንዲንከባከባቸው እና እንዲጠብቃቸው የተሰጣቸው 3 ነገሮች አሉ፡፡ እነሱም፡-

፩. ንብረት፡- በላቡ በወዙ ጥሮ ግሮ የሚያፈራው ሀብቱ ሲሆን ሰውም የገዛ ንብረቱን ሊጠብቅ ይገባዋል፡፡ “ንብረቴ ነው፤ እንደ ልቤ ላባክን” ሳይል በአገባቡ በመጠቀም ዋጋ ሊያገኝበት ይገባል፡፡

፪. ጋብቻ፡- ባልና ሚስት አንድ አካል አንድ አምሳል በመሆናቸው ባል ሚስቱን ሚስትም ባሏን መንከባከብ እና መጠበቅ ያስፈልጋቸዋል፡፡

፫. ሕይወት፡- ሕይወታችን ከእግዚአብሔር የተሰጠን ልዩ ሰጦታ በመሆኑ ልንከባከበው ይገባል፡፡

## ሀ.ሰውን ለመስረቅ የሚያበቁ ምክንያቶች

፩. እግዚአብሔርን አለመፍራት
፪. ምኞት
፫. በሰይጣን ግፊት ማቴ. 19፤18
፬. በድሕነት፣ በችግር
፭. በምቀኝነት
፮. በልማድ የመሳሰሉት የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው፡፡

መስረቅ ከላይ እንደ ተመለከትንው የእራስ ያልሆነ ነገርን ሁሉ የእራስ ለማድረግ መጣር ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ያለባለቤቱ ፍቃድ የሌላውን ንብረት መውሰድ፣ የሰውን ንብረት ተውሶ አለመመለስ፣ የስራ ሰዓትን አለማክበር፣ ስልጣንን ያለአግባብ መጠቅም፣ የህዝብ ሀብትን ማባከን ሁሉ እንደመስረቅ ይታያል፡፡

### ለ. የስርቆት አፈጻጸም

አንድ ሰው ስርቆትን በተለያየ መንገድ ሊፈጽም ይችላል፡፡ ከእነዚህም መካከል በመቀማት (በማስፈራራት)፣ ባለቤት ሳያውቅ በስውር በመውሰድ፣ በማታለል፣ በማስመሰል ወ.ዘ.ተ የሚጠቀሱ የስርቆት አፈጻጸም መንገዶች ናቸው፡፡

ስርቆት በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪም መንገድ ሊፈፀም ይችላል፡፡ ይህም በሚዛን በመበደል፣ የማይፈለግ ዕቃን አስመስሎ በመሸጥ፤ በስራ ቦታም የስራ ሰዓትን አለማክበር፣ ባልሰሩት ሰዓት ገንዘብ መቀበል፣ የሰራተኛን ዋጋ ቀንሶ መክፈል፣ እጅ (በጉቦ) መንሻ መቀበል እና የመሳሰሉት በተዘዋዋሪ የሚፈፀሙ ስርቆቶች ናቸው፡፡

## ሐ. ስርቆት በመንፈሳዊ ቦታ

በእግዚአብሔር ስም እየሰበኩ የምዕመናንን ንብረት ለግል መጠቀም፤ እንደ ይሁዳ ያሰቡ መስለው ለመስረቅ የሚጥሩ በመንፈሳዊነት ካባ ስርቆትን የሚፈጽሙ ናቸው፡፡ ማቴ. 23፥14፣ ሉቃ 20፥47 በተጨማሪም፡-

- .አስራት ባለማውጣት ሚል 3፥8 “ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም። የሰረቅንህ በምንድር ነው? ብላችኋል። በአሥራትና በበኵራት ነው።”

- . ስዕለትን አለማስገባት

ከስርቆት ለመራቅ ማድረግ የሚገባን ጠንክሮ መስራት ነው፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ "የማይሰራ አይብላ" እንዳለ ሰው የራሱ ያልሆነው ነገር ከመመኘት እና ከመፈለግ የላባችንን ውጤት መፈለግና መመገብ ይገባናል፡፡ 1ኛ ተሰ. 4፤12, 2ኛ ተሰ. 3፤10, የሐዋ. 20፤35

## ፬.፫.፰ ትዕዛዝ ፰ *"በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር" ዘጸ 20፤16*

*ውድ አንባብያን ይህ ትዕዛዝ ከአስርቱ ትዕዛዝ በስምንተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከፍቅረ ቢጽ ትዕዛዛት በአምስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በባልንጀራ ላይ በሐሰት አትመስክር የሚለው ትዕዛዝ ባልንጀራችን ላይ በሐሰት እንዳንመሰክር እንደልጓም ሆኖ የሚይዘን ሲሆን የሰዎች ክብራቸው፣ ሕይወታቸው እንዲጠበቅ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው፡፡*

**አፈጻጸሙ፡-** ይህ ትዕዛዝ በተለያዩ መንግዶች የሚፈጸም ትዕዛዝ ነው፡፡ ሐሰተኛ ምላስ፣ ሐሰተኛ ጽሑፍ፣ ሐሰተኛ ፊርማ፣ የሐሰት ዝምታ እና የሐሰት መረጃ በመስጠት ሊፈጽም ይችላል፡፡

### ፩. በሐሰት አትመስክር

ያላዩትንና፣ ያልሰሙትን፣ ያላረጋገጡትን ነገር በትክክል እንደሚያውቁት አድርጎ መናገር መመስከር ነው፡፡ በተጨማሪም ምስጢር ከሆነ ውጭ እውነትን አለመግለጽ በሐሰት እንደመመስከር ይቆጠራል፡፡

### ፪. ሰዎች በሐሰት የሚመሰክሩበት ዋና ዋና ምክንያቶች

1. በይሉንታ
2. በዘረኝነት
3. በጥቅም
4. በምቀኝነት
5. ለውዳሴ ከንቱ
6. በልማድ

ሰው በሐሰት ሲመሰክር፡- የተመሰከረበትን
የመሰከረውንና
የሚመሰክርለትን } ሰው ይጎዳል፡፡

አትግደል፣ አትስረቅ፣ በከንቱ አትማል የሚሉትን ትዕዛዝ የሚያፈርስ ሕግ ነው፡፡ ምክንያቱም ሐሰቱን ለማሳመን በእግዚአብሔር ስም ስንምል፣ በሐሰት የተመሰከረበት ካሳ ክፈል ተብሎ ሲጠየቅ እንዲሁም የሞት ፍርድ ሲፈረድበት በዚህ ህግ መጣስ ሌሎች ህጎችም አብረው ይጣሳሉ፡፡

በሐሰት ዓላማ ተነስቶ፣ በሐሰተኛ ሕልም እና ራዕይ (ትንቢት) ሰዎችን ማታለል ይህንን ትዕዛዝ ማፍረስ ነው፡፡ ክርስቲያን ግን በእውነት ስለ እውነተኛው አምላክ መመስከር ይገባዋል፡፡ "እግዚአብሔር ሐሰትንና የሐሰተኛ ከንፈሮችን በጣም ይጠየፋል፡፡ እውነትን የሚያደርጉ ግን በእርሱ የተወደዱ ናቸው፡፡ ምሳ. 21፤22 ስለዚህ ከትዕዛዙ እንድንጠቀም ማድረግ ይገባናል፡፡

ሰዎችን በሌሉበት በሐሰት ከምናማ በግል ማናገር ይገባል፡፡ ምክንያቱም "የሐሰተኛ ሰው ደሞዙ የዲን እሳት የተመሰለ ሞት ነው" ራዕ. 21፤3 "ውሸታም ሰው እና ስንቅ እያደር ይቀላል" እንዲሉ አበው፡፡

*ውድ አንባብያን ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳለው "መልካም ዘመን ሊያይ የሚሻ ምላሱን ከክፉ ይከልክል" ፩ኛጴጥ 3፤11 ስለዚህ እኛ እውነቱን ተናግረን መልካም የሆነች መንግስቱን ለመውረስ የበቃን ያድርገን፡፡ አሜን፡፡*

## ፬.፫.፱ ትዕዛዝ ፱ *"የባልንጀራህን ቤት አትመኝ"*

"የባልንጀራህን ቤት አትመኝ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውን ገረዱንም በሬ አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማንኛውንም አትመኝ" ዘጸ 20፥17 ይህ የፍቅረ ቢጽ አምስተኛ የሆነው ትዕዛዝ አትመኝ ሲል መመኘት ብቻ ሳይሆን አታስበው አትፈልገው ማለትም መሆኑን ልብ ልንለው ይገባል፡፡ ምኞት የኃጢአት ስራ ናት፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ 1፤2 "ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች ኃጢአትም ካደገች በኃላ ሞትን ትወልዳለች" በማለት የኃጢአት እና የኃጢአት ወጤት የሆነው ሞቱ ምንጩ ክፉ

ምኞት መሆኑን ይገልጻል፡፡ ስው የሌሎችን ሲመለከት(ሲመኝ) ከእግዚአብሔር የተሰጠው መልካሙን ስጦታ መመልከት ያቅተዋል፡፡ ምክንያቱ የእሱ የሆነውን ሀብት የሚመለከትበት በጎ ህሊናው የሰዎችን በመመልከት ስለሚባክን ነው፡፡

- ሰዎች በዝሙት ኃጢአት የሚወድቁት አትመኝ የሚለውን ሕግ ካፈረሱ በኋላ ነው፡፡ ማቴ. 5÷28
- ምኞት ብዙ ጉዳት ያለበት ኃጢአት ነው፡፡ የተለያዩ ኃጢአት ከመፈፀማቸው በፊት በምኞት መስመር ማለፋቸው አይቀሬ በመሆኑ እንድንጠነቀቅ ታዘናል፡፡
- ምኞት ታላላቅ አባቶችን ያሳተ ነው፡፡ አዳም እና ሔዋንን፤ ንጉስ ዳዊት ወዘተ...
- ክፉ ሃሳብ፤ መጥፎ ምኞት በሰው ላይ የሚሰለጥነው ሰውየው ስራ ፈት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ስራ መፍታት ራሱ ለማይገቡ ሃሳቦች ስለሚያገልጥ ራስን በስራ መወጠር ያስፈልጋል ልክ "ስራ ያጣ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል" እንደሚባለው፡፡

## የምኞት አይነቶች

**፩. የስጋ ምኞት**- ለዝሙት፣ ለመብላት፣ ለመስማት የሚደረገውን ጉጉት ያጠቃልላል፡፡
ዘፍ. 25፤29-34 ኤሳው ብኩርናውን የሸጠው በመብል ምኞቱ ነው፡፡ እስራኤላውያንም የምንበላውን ስጋ ማን ይሰጠናል በማለት በልቅሶ የተመኙት በመቅሰፍት ተመተው በዚያ ተቀብረዋል፡፡ ዘኍ. 11፤34 የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ ሲል አታመንዝር ብሎዋል እና ያንተ ለማድረግ አትመኝ ለማለት ነው፡፡
**፪. የገንዘብ ምኞት** - ንጉስ አክዓብ የናቡቴን መሬት ለመውሰድ የበቃበት ምክንያት የገንዘብ(ሀብት) ምኞት በመሆኑ ነው፡፡ የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ ሎሌውንም ገረዱንም አህያውን በሬውን ሁሉ ያንተ ለማድረግ አትመኝ
**፫. የክብር፣ የታዋቂነት፣ የስልጣን፣ የማዕረግ ምኞቶች** - ዲያቢሎስ "ወደ ሰማይ አርጋለሁ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ክዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ... በልዑልም እመሰላለሁ" በማለት በመመኘቱ ነው ለታላቅ ውርደት የበቃው፡፡ ኢሳ. 14፤13 አዳምና ሔዋን ክፉንና ደጉን ለማወቅ እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ካላቸው ጉጉት እና ምኞት የተነሳ ለታላቅ ውድቀት በቁ፡፡ ዘፍ. 3፤5
ከክፉ ምኞት ለመራቅ መፍትሔው ለዚህ ዓለም እንግዳ መሆናችንን አውቀን ከንቱ የሆነውን የምኞት ምንጭ መናቅ፣ መተው እና መሸሽ ነው፡፡ "ዓለሙም ምኞቱም ያልፍልና" መክ. 1፤10, ዮሐ. 2፤1

## ፩.፫.፲ ትዕዛዝ ፲ "ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ" ዘሌ. 19፤18

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ 19፤17-19 ሕግም ነቢያትም በ2ቱ ሕግ እንደሚጸኑ እነዚህም እግዚአብሔርን በፍፁም ልብ በፍፁም ነፍስ መውደድ እና ባልንጀራን እንደራስ አደርጎ በመውደድ የሚጠቃለል መሆኑን አስተምሯል፡፡
**ባልንጀራ** ፡- የምንለውም ምስጢር የምንነግረው ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የአዳም ልጆችን(የሰው ዘር ሁሉ) የሚያጠቃልል ሲሆን ሁሉምንም ግብዝነት በሌለው ከእውነተኛ ፍቅር በመነጨ መዋደድ ልንወድ ይገባል፡፡
የክርስቲያኖች ፍቅር ጠባያዊ ወይም መነሻ ባለው ጥቅም መሆን አይገባውም፡፡ ይህም ጥቅም ምንጭ ሳይሆነን ባልንጀራችን መልካም ስላደረገልን ብቻ ሳይሆን ምንም ያላደረገልንን ወገናችንን እንዲሁም ጠላታችንንም እንኳን ቢሆን ጌታችን በተግባር እንዳሳየን፤ ሁሉንም በአንድ አይን በመመልከት የቅርቡንም የሩቁንም ወዳጅንም ሆነ ጠላትን መውደድ እንደሚገባን ያስተምረናል፡፡ ለባልንጀራችን ያለን ፍቅር ከልብ የመነጨ ስሜት ብቻ ሆኖ መቅረት አይገባውም፡፡ ይህም ባልንጀራችንን በስጋዊና በመንፈሳዊ ሕይወት በመርዳት በተግባር መግለጽ ይገባል፡፡ ለምሳሌ:-

| በሥጋ ሕይወት | በመንፈሳዊ ሕይወት |
|---|---|
| - ለኑሮ የሚያስፈልገውን ምግብ፣ መጠለያ፣ ልብስ በመለገስ | - በጸሎት በማሰብ 2ኛ ጢሞ. 1÷3 |
| - መብቱ እንዲጠበቅ በማድረግ | - አርአያ በመሆን፤ ወደ ቤተ-እግዚአብሔር ማቅረብ ማቴ. 5÷16, 1ኛ ጴጥ. 5÷3 |
| - ጉዳት እንዳይደርስበት በመከላከል | - በመንፈሳዊ ምክር በማነጽ የሐ. 15፤3 |
| | ሮሜ. 12፤8 |

ፍቅር በዚህ ከላይ በጠቅስናቸው በጎ ተግባራት ብቻ የሚውስን ሳይሆን እራስን አሳልፎ እስከ መስጠት ድረስ ሊቀጥል ይገባዋል፡ "ነፋሱን ስለወዳጆቹ አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም፡፡" ማቴ.15፤16 ዮሐ. 15፤13

**እንደራስ መውደድ**

- ❖ ኤፌ. 5፥30 የገዛ ሰውነቱን የሚጠላ እንደሌለ ሁሉ ራሳችንን በምንወድበት ሌላውን መውደድ እንደ ሚገባን በግልፅ ያስረዳል፡፡
- ❖ ማንም መዋረድን ውድቀትን በራሱ ላይ ክፉ ነገርን የሚፈልግ እንደሌለ ሁሉ ለራሳችን ሊደረግልን የምንፈልገውን ለሌለው ማድረግ እንደ ሚገባን በማቴ. 7፥12 ላይ በጉልህ ተጠቅሷል፡፡
- ❖ ባልንጀራውን በእውነት የሚወድ ባልንጀራውን በሥጋም በነፍስ አይገለውም፤ ንብረቱን አይሰርቀውም፣ በሐሰት አይመሰክርበትም ፣ንብረቱንና ቤቱን በክፉ በመመኘት አይመቀኘውም፡፡ ሮሜ. 13፥8-10
- ❖ 1ኛ ዩሐ. 3፥14-18 "…. ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍስ ጉዳይ ነው… ወንድሙ የሚያስፈልገውን ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል? በሥራ እና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ"
- ❖ ስለዚህ ሁላችንም የክርስቶስ አካል እንደመሆናች፤ ከአካለችን አንዱ ቢታመም አታስፈልገኝም እንደማንል ሁሉ የሌላው ሃዘን የእኛ፤ ደስታቸውም የእኛ ሊሆን ይገባዋል፡፡

**ማጠቃለያ**

*ውድ አንባብያን የሰው ልጅ በተሰጠው ልቦናዊ ህግ እየተመራ ለዘላለም ለፈጣሪው ለእግዚአብሔር እየተገዛ መኖር ስላቃተው ለፍጥረቱ የሚራራ ልዑል እግዚአብሔር የጽሑፍ ህግ በሲና ተራራ በሙሴ አማካኝነት ለፍጥረቱ ሰጠ፡፡ ይህ ጽሑፋዊ ህግ አስርቱ(10ቱ) ትዕዛዛት በመባል ይጠራል፡፡ 10ቱ ትዕዛዛት በፍቅር ሲከፈሉ በሁለት(ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቀረ ቢጽ)፣ በአተገባበር ሲከፈሉ በሶስት(በመስራት፣ በመናገር እና በማሰብ) መሆኑን ተመልክተናል፡፡ በአጠቃላይ የእግዚአብሔር ቅዱስ ህዝብ ከሌላው አረማዊ ህዝብ ሰለሚለይ ከክፉ ስራ የሚከለክል፣ ወደ መልካም ስራ የሚመራ የጽሑፍ ህግ ተሰጠው፡፡*

## <u>**መልመጃ ሁለት**</u>

**ትዕዛዝ ፩** ባዶ ቦታውን ሙሉ

፩. ______________________የሰዎች ክብራቸው፣ ሕይወታቸው እንዲጠበቅ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው፡፡

፪. እውነተኛ ፍቅር የሚገለጠው በ __________________________ ነው ፡፡

፫. ______________________________አታመንዝር ላለው ሕግ ፍጻሜ ነው፡፡

፬. ______________________ከአስርቱ ትዕዛዝት መካከል የፍቅረ ቢጽ መጀመሪያ ትዕዛዝ ነው፡፡

፭. ______________________ማለት በእግዚአብሔር የተናቀ የማይጠቅም የማይረባ ማለት ነው፡፡

**ትዕዛዝ ፪ እውነት ሀሰት በማለት መልሱ**

፩. ስዕለትን አለማስገባት እንደ ስርቆት ይቆጠራል ፡፡

፪. እግዚአብሔር አምላካችን አዳምና ሔዋንን ፈጥሮ «ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሏት፡፡» በማለት ባርኳቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት የቅዱስ ጋብቻ ተቀዳሚ ዓላማ ዘር ለመተካት ነው፡፡

፫. አንድ ክርስቲያን በሐሰት መስክሮ ነብስ ቢያድን ወይም ሰው ቢያስታርቅ መልካም ስራ እንደ ሰራ ይቆጠራል፡፡

፬. ሃይማኖትን መካድ የአመንዝራነት መገለጫ ነው፡፡

፭. የአይሁድ ሰንበት ጽድቅን በመስራትና በመቀደስ ትከብር ነበር፡፡

፮. አንድ ሰው ሰውን የሚገድለው በማጣቱ ነው፡፡

፯. የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት ለስሙ ክብርን ካለመስጠት የሚመጣ ነው፡፡

፫. አትግደል የሚለው ሕግ የራስንም ሕይወት ጨምሮ ማንኛውንም ግድያ ያካትታል፡፡

**ትዕዛዝ ፫ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አብራሩ**

፩. ዝሙት፣ አመንዝራነት፣ ሴሰኝነት፣ ትርጉማቸውን በማብራራት አስቀምጡ?

፪. ሰንበተ ክርስቲያን የምትባለዋ  የትኛዋ ናት? አብራሩ፡፡

፫. የእግዚአብሔርን ስም ከንቱ የሚያደርጉ ነገሮች ምንድን ናቸው?

፬. አትግደል የሚለውን ሕግ ከባድ የሚያደርገው ምክንያት ምንድን ነው?

## ምዕራፍ አምስት

## ፩. ፮ቱ ሕግጋተ ወንጌል

*ውድ አንባብያን ከዚህ በፊት ባለው ምዕራፍ እስራኤላውያን ከግብጽ ምድር ከባርነት ቀንበር ተላቀው የተሰፋይቱን ምድር(ከነዓን) ለመውረስ በሚያደርጉበት ጉዞ ወቅት የተሰጠውን አስርቱ (10ቱ) ትዕዛዛትን በዝርዝር ለማጥናት ሞክርናል፡፡ በዚህ ምዕራፍ በሐዲስ ኪዳን የህግ ሰሪ የሆነው ጌታችን አምላክች መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ ሲያስተምር በሙሴ አማካኝነት የሰጠውን የብሉይ ኪዳን ህግ በማጣቀስ ሐዲስ የመሰረተልንን የፍቅር ሕግ እናጠናለን፡፡ ይህ ህግ ስድስቱ (6ቱ) ህግጋተ ወንጌል ተብሎ ይጠራል፡፡ አንዳንድ መምህራነ-ወንጌል በዚህ ምዕራፍ ላይ የተዘረዘሩትን ህጎች 6ቱ ቃላተ ወንጌል በማለት የሚያስተምሩ አሉ፡፡ ነገር ግን ትዕዛዛቱ ከይዘታቸው አንጻር ስንመለከት የሕግ ባሕርይ ስላላቸው ስድስቱ ሕግጋተ ወንጌል ተብለው ተጠቅሰዋል፡፡ ከስድስቱ ህግጋተ ወንጌል ጋር መልካም ቆይታ!!*

### ፩.፩ «አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል፡፡ እኔ ግን እለችኋለው በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ፍርድ ይገባዋል፡፡» ማቴ 5፥ 22

የክርስትና ህግ የፍቅር ህግ ነው፡፡ ጌታችን በወንጌል ያስተማረን ጠላቶቻችንን እንኳን ማፍቀር እንዳለብን ነው፡፡ ሰለሆነም የጥላቻ መገለጫ የሆኑትን ነገሮች ማሶገድ ይገባናል፡፡ ይህም ትዕዛዝ የሚያስተምረን ፍቅርን ነገር ነው፡፡

- እኔ ሲል፡- በኦሪት በሙሴ ላይ አድሮ ሕጉን መስራቱንና ወንጌልንም እርሱ እንደሰራና እንደፈፀመ ሲያመለክተን ነው። ዘጸ 20፥13
- በሐዲስ ኪዳን መግደል ሳይሆን ወንድምህን በከንቱ በማስቆጣት፣ በማሳዘን፣ በመሳደብ ለሞት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች ላይ በር ዝጋ ሲል ነው፡፡
- ወንድሙን ጨርቅ ለባሽ ብሎ የተሳደበ የሸንጎ(በአደባባይ) ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ ብሎ የሚሳደብ ፈጣሪውንም የሰደበ በመሆኑ በገሃነም ይፈረድበታል፡፡
- መባህን ስታቀርብ የተጣላኸው፣ ያሳዘንከው እንዳለ ትዝ ካለህ መባውን ከደጀ ሰላም አስቀምጥና አስቀድመህ ከወንድምህ ጋር ተወቃቅሰህ ታረቅና መባህን(ጸሎትህን) ፈጽም፡፡ «ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ስርቆት እንዳይሆንብን፡፡» እንዲሉ አበው
- ከክርስቲያን አንደበት ለጥል የሚያነሳሳ ቁጣ፣ ርግማ፣ ስድብ ሊደመጥ አይገባም፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው ሕገ እግዚአብሔርን ሲያፈርስ ፤ ሕይወቱ ከመንፈሳዊ መስመር ሲወጣ፣ ሥነ ምግባሩ ሊበላሽ ሲል፣ መምከር መገሰጽ እና መቆጣት ተገቢ ነው፡፡

### ፩.፪ "አታመንዝር እንደተባለ ሰምታቸኋል፡፡ እኔ ግን እለችኋለው ወደሴት ያየ የተመኛትም ያን ጊዜ ከእርሷ ጋር አመነዘሯል፡፡ ማቴ. 5፥2

- አታመንዝር ላለው ሕግ ፍጻሜ ነው፡፡

- ሰው በተግባር ብቻ ሳይሆን በልቡም ማመንዘር እንደማይገባውና በልብ ማመንዘርን ሊያመጡ በሚችሉ በስጋዊ የፍቶት ሀሳብ በዓይን በማየት፣ በእጅ በመዳሰስ፣ በመተቃቀፍና በእግር በመጨፈር ሴት (ወንዱን) ከተመኘ በልቡ አመንዝሯል፡፡

- በዚህ ትዕዛዝ መሰረት ሴትን(ወንድን) ማየት ሳይሆን ኃጢአት የሚሆነው አይቶ ለፈቃደ ሥጋ መመኘት ነው፡፡ ምናልባት በተግባር ያልፈጸመው/ችው ሁኔታዎች፣ ጊዜና ቦታ ስላልተመቻቸ ይሆናል፡፡ ስለዚህ አሰናካይ የሆኑትን የዝሙት ዓይኖች እጆችና እግሮቻችን ማስወገድ ይገባል፡፡ ት.ኤር 17፤10

- ቀኝ ዓይንህ፣ እጅህ፣ ከሕዋሳቶችህ መካከል እግርህ ብታስትህ ቆርጠህ ጣላት ሁለት አካል ኑሮህ ገሃነም እሳት ከምትገባ አንዱን አካል አጥተህ መንግስተ ሰማያትን ብትወርስ ይሻልሃል፡፡ ይህ ማለት በነዚህ የስሜት ህዋሳት አማካኝነት ከሚመጡ ኃጢአቶች በመቆጠብ ራስን መግዛት ያስፈልጋል ማለት ነው እንጂ በቀጥታ አይንህን አጥፋ እግርህን ቁረጥ ማለት አይደለም፡፡ እንደ ስምዖን ጫማ ሰፊው፣ ቅዱስ አትናትዮስ ዘአንፆኪያ እና አባ መርትያኖስ፡፡

- አይቶ ሰምቶ ስሜትን ለልቡና ሳይሰጡ ያለፉት ከሆነ ኃጢያት አይሆንም፡፡

## ፩.፫ "ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ የተፈታችውንም ያገባ አመንዝሯል" ማቴ. 5፤32

- ጋብቻ ልዑል እግዚአብሔር የመሰረተው ታላቅ ምስጢር እንደ መሆኑ መጠን ያለበቂ ምክንያት በቃል ኪዳን የታሰረውን በራሳቸው ፍቃድ መለያየት አይችሉም፡፡ ማቴ. 19፤26

- ሚስቱን ያለዝሙት ምክንያት የፈታ/የፈታች እንድትሴስን/እንዲሴስን፣ ከሕግ ውጪ እንድትሆንም ምክንያት የሆነ በደሉ ከፍተኛ ነው፡፡

ዝሙት በሁለት ይከፈላል
- 1ኛ ከሃይማኖት ውጪ መሆን (መካድ)፤ ሃይማኖት መለወጥ ጣዖት ማምለክ
- 2ኛ አመንዝራነት- ባል ከሚስት፣ ሚስትም ከባል ውጪ መሔድ

- በዝሙት ምክንያት የተቀደሰውን ጋብቻ ያፈረሰ ወይም ያሰናከለ የክርስቶስ እና የቤ/ክንን ሕብረት የካደ እንዲሁም ቃል ኪዳኑን የረገጠ በደሉ ነው፡፡ ተጸጽቶ ንስሐ ካልገባ በስተቀር ከክርስቶስ ሕብረት የተለየ ያደርገዋል፡፡

- በዝሙት ምክንያት የተፋታው ወይም የተፋታችው ንስሐ ሳይገባ ሌላ ካገባ/ች ማመንዘር ይሆንበታል/ባታል፡፡ ስለዚህ ከማግባቱ በፊት በዝሙት የተፈታችው ንስሐ መግባቷን በንስሐ አባቷ ምስክርነት ማረጋገጥ አለበት ወይም አለባት፡፡

*ውድ አንባብያን ከጌታ ጋር ያለን አንድነት እንዳይፈርስ ጋብቻን(ቃል-ኪዳንን) እስከ ሞት ጠብቆ መያዝ ይገባናል፡፡*

## ፩.፬ "እኔ ግን እላችኋለው ከቶ አትማሉ" ማቴ. 5፤34

*ውድ አንባብያን መሐላ ማለት አንድን ነገር ምስክር ኢድርጎ መጥራት ነው፡፡* ቅዱስ ጳውሎስም በዕብ. 6፤16 "ሰዎች ከእርሱ በሚበልጠው የምላሉና ለማስረዳትም የሆነው መሐላ የሙግት ሁሉ ፍፃሜ ይሆናል፡፡ ይህም እውነቱን ለማስረዳት ግዴታ ሆኖበት የእግዚአብሔርን ስም ዋስ በማድረግ ስሙን ቢጠራ (ቢምል) ኃጢአት አይሆንም፡፡"

ከቶ አትማሉ ሲል በሆነው ባልሆነው፣ ከንቱ በሆነው ነገር፣ በትንሸ በትልቁ፣ በማንኛውም ሁኔታ ያለአስገዳጅ ምክንያት እውነትን ለመግለፅም ቢሆን እንኳን መማል እንደ ማይገባ ትዕዛዙ ያስረዳናል፡፡ ምክንያቱም ሰማይ ዙፋኑ ነው፡፡ ምድርም የእግሩ መረገጫ ናት፡፡ እኛም ብንሆን የእጆቹ ስራ ነንና በማንኛቸውም ነገር ጠቅሰን መማል ክልክል መሆኑን አስረግጦ ያስረዳናል፡፡ ስለዚህ እውነት ለሆነው አዎ ትክክል ላልሆነው አይደለም ማለት በቂ እንደሆነ ጌታችን ተናግሯል፡፡ ማቴ. 5፤37, ያዕ. 5፤12

## ፩.፭ ክፉን በክፉ አትቃወሙት ማቴ. 5፤38

ክፋት የዲያቢሎስ ነውና ማንኛውም ነገር በትዕግስት በበጎ ምግባር ማሸነፍ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ክፉውን ሰው መልሶ በክፉ መቃወም በክፋቱ መተባበር ነው፡፡

በኦሪት ህግ ዓይን ያጠፋ ዓይኑ ይጥፋ የሚል ሕግ ነበር፡፡ ጌታችን ሲያጸናልን «ቀኝ ፊትህን ቢመታህ ሁለተኛውን መልስለት፣ መጎናፀፊያህን ሊወስድ ቢመጣ ቀሚስህን ደርበህ ስጠው» ማቴ 5፤39 ብሎ የሕጉን አፈጻጸም አስቀመጠልን፡፡

*ውድ አንባብያን የአባቶቻችን ህይወት የወንጌል ፍሬ ነውና የሚከተለው ታሪክ ይህንን ይመሰክራል፡፡ አንድ አባት በቤታቸው እንግዶችን ተቀብለው ያሳዳራሉ፡፡ በአንድ ወቅት እንደተለመደው እንግዶችን ተቀብለው ሲያሳደሩ እንግዶቹ ሌቦች ሆነው ኖሮ በሌሊት ያላቸውን ንብረት ሁሉ ዘርፈው ሲሔዱ ሁለት ዲናር የምታወጣ ፀምር በመርሳታቸው እኚ አባት ይህቺን ረስታቹሃል ውሰዱ ሲሏቸው ሌቦቹ ይህን በማድረጋቸው በድርጊቱ በእጅጉ ተፀፅተው ንብረቱን መልሰው ንስሐ ገብተው ወደ ፅድቅ ስራ ተመልሰዋል፡፡ ክፉውን በበጎ በመመለሳቸው ሌቦቹን ወደ ቅድስና ሕይወት ለመመለስ ችለዋል፡፡*

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሲቃወሙት፣ ሲሰድቡት፣ ሲያሰቃዩት እርሱ መልሶ አልተሳደበም ይልቁኑ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው በማለት ተናገረ፡፡ ማቴ. 27፤12-14 1ኛ ጴጥ 2፤23

ይህ ሕግ የክርስቲያን ፍፁምነቱ የሚረጋገጥበት ፍኖተ ጽድቅ ነው፡፡ ትዕግስትን ገንዘብ አድርገን ሌላው ክፉ ላደረገብን በእኛ በጎ አፀፋ ተፀፅቶ እንዲመለስ የሚያደርግ፣ ክፉዎችን ከምንቃወም መጸለይ እንደሚገባን የሚያስረዳን ነው፡፡

## ፭.፮ "እኔ ግን እላችኋው ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሟችሁን መርቁ(ባርኩ) ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ ስለሚበድሏችሁም ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ" ማቴ. 5፤44

እውነተኛው ፍቅር የሚገለጠው ጠላትን በመውደድ ነው፡፡ ወዳጅን መውደድ ከባድ ስላልሆነ እግዚአብሔር አባታችን ጎዳኤ በቀል (ይቅርባይ) እንደሆነ ሁሉ እኛም እንደ ልጅነታችን በተግባር ሲሰድቡን መመረቅ፣ ቂም ባለመያዝ፣ በቀል ሳይኖርብን በትዕግስት በመቻል ማሳለፍ እንደሚገባን ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መማር አለብን፡፡ ጌታችን እኛ ጠላቶቹ ሳለን እስከ መስቀል ሞት ያበቃው ፍቅር ነው፡፡ ሮሜ 5፤8 ቆላ 1፤2-22

"እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል" 1ኛ ዮሐ3፥16

እግዚአብሔር በኃጥአንም በፃድቃንም ላይ ፀሐይን እና ዝናብን እንደሚያፈራርቅ ሁሉ የእኛም ፍቅር ያለአድልዎ ሁሉንም በአንድ ፍቅር መውደድ አለብን፡፡ የሚወዱንን ብቻ ከወደድንማ ከአሕዛብ በምን ተለየን ስለዚህ አምላካችን ሁሉንም በመውደድ ፍፁም እንደ ሆነ እናተም ፍፁማን ሁኑ ብሎ ደምድሞታል፡፡

ውድ አንባብያን ተከታዮቹ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዳግም ምጽአቱ ጊዜ የሚጠይቃቸው ጥያቄዎች ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ይባላሉ፡፡ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፦

# ፮ቱ ቃላተ ወንጌል

፩. ተርቤ አብልታችሁኛልና፥

፪. ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥

፫. እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥

፬. ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥

፭. ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥

፮. ታስሬ ወደ እኔ መጣችኋልና

*"ጻድቃንም መልሰው ይሉታል። ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ? እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ? ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን? ንጉሥም መልሶ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።" ማቴ. 25፤35-40*

## <u>ዋቢ መጻሕፍት</u>

፩. ሕግጋተ እግዚአብሔር --------------------- በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ

፪. ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ---------------------- አባ መልከጼዴቅ

፫. ማኅበራዊ ኑሮ በኢትዮጵያ ----------------------- አባ መልከጼዴቅ

፬. ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ------------------------- ማኅበረ ቅዱሳን

፬. መጽሐፍ ቅዱስ